# የቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ክዋኔ አውድ

ደስታ አማረ


**አጽህሮተ ጥናት**

ፎክሎር ህዝቦች በመኖሪያ አካባቢያቸውና በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች ሁሉ ሲገናኙ የሚከውኑዋቸው ወጎች፣ እምነቶች፣ ህዝባዊ ጥበቦችንና ሌሎችንም ያካትታል። ከነዚህ አንዱ የሆነው የስም ስያሜ አንድ ህፃን ከነበረበት ደረጃ ወደ ተከታዩ ወይም ወደ ሌላ ደረጃ መሻገሩንና ወደ ማህበረሰቡ መቀላቀሉን ያመለክታል። ይህን መሰሉን የደረጃ ሽግግር የሚያመለክተው ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል፣ በቦረና ዞን በሚገኘው ቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል (ጉቢሳ) ላይ ያተኩራል። ቦረናን ጨምሮ የኦሮሞ ባህልና ወግ በአብዛኛው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየው በቃል ነው፡፡ እነዚህ በቃል ያሉ አብዘኛዎቹ ባህልና ወጎች ወይም የፎክሎር ዘርፎች አልተጠኑም። በባህሪ ተለዋዋጭ በመሆናቸው በቃል ሲያስተላልፉ የነበሩት የህዝቡ ባህላዊ፣ ማህበራዊና መንፈሳዊ እውቀቶችና እሴቶች፣ ይለወጣሉ፣ ይረሳሉ፣ ይጠፋሉ። ስለዚህ አነዚህ አሁን በመከወን ያሉና የመለወጥ እድላቸው ሰፍቶ የሚታዩ ባህላዊ ክዋኔዎች ተጠንተው በጽሑፍ ቢቀመጡ ነባሩን እውቀት ለትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል። በመሆኑም ይህ ሀሳብ ለጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ሆኗል። በጥናቱ የቦረና አሮሞዎች የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ሲያከብሩ ምንምን ክዋኔዎች ይከውናሉ? በየክዋኔዎቹ ምንምን የፎክሎር ዓይነቶች ይቀርባሉ ወይም ይካተታሉ? በየክዋኔዎቹ ውስጥ የህዝቡ ተሳትፎ ምን ይመስላል? የሚሉት ጥያቄዎች ተመልሰዋል። የጥናቱ ዋና ዓላማ የቦረና ኦሮሞ ማንነትና አተያይ ማሳያ ከሆኑት የባህል ዘርፎች ውስጥ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ክዋኔዎች በውስጣቸው ከያዙት የፎክሎር ዓይነቶች፣ ከሚኖራቸው ተምሳሌታዊ ፍችና ከሚያስተላልፉት መልዕክት አንፃር በመግለፅና በመተንተን መዝግቦ ማቆየት ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት በባህል እውቀታቸው የላቁ ናቸው ተብለው ከሚታወቁት አባቶች ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በታላሚ ናሙና ከተመረጡ በኋላ፣ (1)በቃለመጠይቅ (2) በምልከታ እና (3) ተሳትፎ ምልከታ ዘዴዎች መረጃዎቹ ተሰብስበዋል። ፎክሎር በባህሪው ዘርፈ ብዙ የጥናት ክፍል በመሆኑ የተለያዩ የትንተና አንፃሮች በጥምር መጠቀም ይጠይቃል። ስለሆነም ለዚህ ጥናት መረጃዎች መተንተኛ በዋንኛነት የተመረጡት የአውድና የክዋኔ የትንተና አንፃሮች ናቸው፡፡ በነዚህ የትንተና አንፃሮች በክዋኔዎች ሂደታዊ አፈፃፀም ባለጉዳዩ የመለየት፣ የሽግግር እና የመቀላቀል ደረጃዎችን ሲሻገር እንዲታይ፣ ክዋኔዎቹና በየክዋኔዎቹ የሚቀርቡት የፎክሎር ዓይነቶች ምንነትና ፍካሬያዊ ትርጓሜያቸውም እንዲሁ ጎልተው እንዲወጡ ተደርገዋል። ባጠቃላይ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ጉቢሣ የተለያዩ የፎክሎር ዓይነቶች ማለትም ሥነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ትውን ጥበባትን አካቶ በመያዝ የቦረናን ኦሮሞ እምነት፣ አተያይ፣ ጠንካራ የርስ በርስ ግንኙነት፣ የምጣኔ ሐብት አገነባብ ዘዴዎችና የባህል ህግጋት ጥበቃ ዘዴዎቹ ጎልተው እንዲታዩ ያደረገ በዓል ነው፡፡


**ቁልፍ ቃላት፡** ቦረና፣ ጉቢሳ፣ ክዋኔ

## 1.መግቢያ[1]

ቦረና በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ዞኖች አንዱ ነው። ዞኑ ይህን መጠሪያውን ያገኘው፣ በውስጡ ከሚኖረው የቦረና ኦሮሞ ነው፡፡

የዞኑ ጠቅላላ የመሬት ስፋት 56,000 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ሲሆን፣ የዚህ ስፋት 80 በመቶ ለከብት ርቢ /ለግጦሽ/ የሚውል ነው፡፡ ለእርሻ ማዋል ይቻላል የሚባው የዞኑ መሬት ደግሞ 1,176,288 ሄክታር ነው፡፡(OBPED,2000:250)

በዞኑ የሚኖረው ህዝብ ብዛት እ.አ.አ በ2007 በተደረገው የቤትና የህዝብ ቆጠራ መረጃ መሠረት 962,489 ሲሆን ከዚህ ቁጥር ውስጥ 487,074 ወንዶች፣ 475,465 ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ የዞኑን ውሃ ሀብት ቢሮ የ2003 ሪፖርት ደግሞ የህዝቡን ቁጥር ወደ 1.1 ሚሊዮን ያደርሰዋል፡፡

### ምጣኔ ሐብት

የቦረና ህዝብ ምጣኔ ሐብት የተመሠረተው በከብት ርቢ ላይ ሲሆን፣ በርቢው ውስጥ ከብቶች፣ በጎች፣ ፊየሎች፣ ዶሮዎች እና ሌሎች እንደ ግመል የመሳሰሉት እንደ አየር ንብረቱ ሁኔታ ይካተታሉ፡፡ ከከብት ሪቢው ጎን ለጎን በቆሎ ጥራጥሬና ስንዴም ያመርታሉ፡፡ አብዘኛው ህዝብ ወተትና ሌሎች የእንስሳት ተዋፅኦን የሚመገብ ሲሆን ለከብቶቻቸውም መኖ በማሳ ላይ ያዘጋጃሉ፡፡

### ማህበራዊ መዋቅር


ቦረና በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡ ሰቦና ጎና፣ እነዚህ ዋና ዋና ክፍሎች በመላው ቦረና ውስጥ የሚኖሩ ሲሆኑ፣ በገዳ ሥርዓት ውስጥ እኩል ቦታ አላቸው[2] ሁለቱ ክፍሎች እንደገና በንዑሳን ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡ ክፍፍሉ “Balbala” እስከሚባለው ደረጃ ድረስ ይወርዳል፡፡

---

[1] ይህ ጥናት በ2000 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪዬ “በቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል አከባበር ፎክሎራዊ ገፅታ” በሚል ርዕስ በሰራሁት ጥናት አንድ ንዑስ ርዕስ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ ባህሉ በአሁኑም ጊዜ እዚህ ጥናት ውስጥ በተመለከተው መንገድ እንደሚከወን በተለያዩ ሥራዎች አጋጣሚ ማየት ችያለሁ፣ ከክልሉና ከዞኑ ባህልና ቱሪዝም መሥሪያቤቶችም በስልክ ማረጋገጥ ችያለሁ።

[2] ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.፤Asmarom:1973:11

አከፋፈላቸው የሚከተለውን ይመስላል፡




(ቦርቦር ቡሌ ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 24 ቀን 1999፣ Gammachu, 2002:35)

### ጋብቻ

በቦረና በጋብቻ አማካይነት የሚደረገው ግንኙነት የሚወሰነው ዝምድና መኖር አለመኖሩ ከተጠና በኋላ ነው። ሁለቱ የቦረና ዋና ዋና ክፍሎች (ሰቦ እና ጎና) ሊጋቡ ይችላሉ። በአንፃሩ ግን ጎና ከጎና፣ ሰቦ ከሰቦ አይጋቡም። ሰቦ ለሰቦ ወንድምና እህት ሲሆን በባህሉ ሰቦ ለጎና አማች ነው። (Gemechu 2002:35) ። በቦረና ከፍተኛ ቦታ ክብር ተሰጥቶት የሚከወነው የጋብቻ ሥርዓት በሽምግልና በሁለቱ ቤተሰብ ስምምነት ሂደቱን ተጠብቆ የሚፈፀመው ጋብቻ ነው።

### ሃይማኖት

ከቦረና ኦሮሞ አብዛኛው የገጠር ነዋሪ ነባር የሆነውን የኦሮሞ ሃይማኖት የሚከተል ሲሆን በከተሞች ነዋሪ የሆኑት ብዙዎችና የገጠሩ ጥቂቶቹ የተለያዩ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። የነባር ሃይማኖቱ ተከታዮች በአንድ ፈጣሪ "Waaqaa" የሚያምኑ ሲሆኑ፣

ሰላም እንዲኖር፣ ደምኖ እንዲዘንብ፣ ከብቶች እንዲረቡ፣ ትውልድ እንዲቀጥል ይህንኑ "Waaqaa" ይማፀናሉ፡፡ እምነቱም ዋቄፈና (Waaqeffannaa) በሚባል መጠሪያው ይታወቃል፡፡

**አስተዳደራዊ ሥርዓት-ገዳ**

ገዳ የኦሮሞ ህዝብ ከጥንት ጀምሮ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወቱን ይመራበት የነበረ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው፡፡ የገዳ ሥርዓት በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተግባራዊ መደረግ እንደጀመረ የሚገልፁ መረጃዎች አሉ፡፡ በቃል ያሉት መረጃዎች ደግሞ በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አከባቢ ኦሮሞዎች የተዳደሩበት እንደነበር የሚገልፅ ነው፡፡ (Tadhi, 2007፡3)፡፡

በሥርዓቱ በየስምንት ዓመቱ ሥልጣን እየተረካከቡ ህዝቡን የሚያስተዳድሩ አምስት የገዳ ክፍሎች (ፓርቲዎች) ናቸው፡፡ እነዚህ አምስት ፓርቲዎች በተለያዩ የኦሮሚያ ዞኖች በተለያየ ስም የሚጠሩ ሲሆኑ በቦረና ተለይቶ የሚተወቀው በየስንት ዓመት ስልጠን እየተቀባበሉ ባለፉት አምስት የመጀመሪያዎቹ አባገዳዎች ስም ነው፡፡ እነሱም ቦሩ ገልማ፣ መዳ ገልማ፣ ሊበን ጀልዴሣ፣ አዲ ጋዮና አሬሮ ጌዶ ናቸው፡፡ በየአስተዳደር ዘመኑ ፓርቲውን የሚመሩ ዋናና ረደት አባ ገዳዎች አሉ፡፡

በቦረና ህዝቡን የሚያስተዳድረው ገዳ በሦስት ይከፈላል፡፡ የመጀመሪያውና ህዝቡን በዋናነት የመያስተዳድረው አርቦራ ገዳ (Gadaa Arbooraa) የተባለው ነው፡፡ ሌሎች ሁለት ገዳዎች ደግሞ የዚህ የዋናው ገዳ ቅርንጫፎች /አካል/ ናቸው፡፡ እነርሱም በንዑሳ ጎሳዎች ስም የሚጠሩ የሀወጡና የኮኒቱ ገዳ ናቸው፡፡ ሁለቱ ቅርንጫዎች ተጣምረው ኮንቶማ ገዳ (Gadaa Kontomaa) ይባላሉ፡፡ ሦስቱም አንዳንድ አባገዳና ረዳት /ኤክስፐርት/ አላቸው፡፡ በአንድነት ስድስቱ የቦረና ገዳ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች፤ አዱላ "Aduulaa" በመባል ይታወቃሉ[3]

በውልደት ታላቅ ነው ተብሎ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ የሚነገርለት የቦረና ኦሮሞ የማንነቱ መለዮ የሆኑ የተለያዩ የባህል ገፅታዎች አሉት፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ባህላዊ ገፅታዎች በየጥናቱ እንደሚከወኑ ከመጥቀስ ያለፈ ሰፋ ያለ እና እራሱን የቻለ ጥናት አልተካሄደባቸውም፡፡ ከነዚህ ካልተጠኑ የባህል (የፎክሎር) ገፅታዎች መካከል አንዱ ጉቢሳ (Gubbisaa) - የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ነው፡፡ የቦረና ኦሮሞ ለስም አሰያየም ደረጃ ወስኖ የሚከውነው ሲሆን፣ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ ልዩ ትኩረትና ቦታ የሚሰጠው ነው። ይሁን እንጂ የህዝቡን ባህል ያጠኑ የውጭ ተመራማሪዎች የበኩር ልጅ ስም ስያሜን በደፈናው ገልፆ ከማለፍ ውጭእንዴት እንደሚከወን፣ በየከዋኔዎቹ ምን ምን ፎክሎራዊ ገፅታዎች በውስጡ እንደሚታዩ በጊዜና በቦታ ለይተው፣ ያመለከቱበት ጥናት አላጋጠመኝም፡፡ በመሆኑም ይህን ጥናት ለማካሄድ ዋና አነሳሽ ምክንያት ሆኗል።

[3] ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999፡፡

### 1.1 ዓላማ

የቦረና ኦሮሞን የበኩር ልጅ ስም ስያሜ ሥርዓቶች ምንነት፣ አፈፃፀማቸውን፣ በበኩር ልጅ ስም ስያሜ ወቅት የሚዘጋጀውን በዓል አከዋወን መመዝገብ፣ በበዓሉ አጋጣሚ በሚከወኑት የፎክሎር ዝርያዎች ላይ ትንታኔ መስጠት የጥናቱ አቢይ ዓላማ ነው፡፡

### 1.2 የጥናቱ አስፈላጊነት

የቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜና ለስያሜው የሚዘጋጀው በዓል አከባበር መጠናቱ የህዝቡን ማበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት፣ አመለካከቱን ለይቶ ለማወቅ ለሚሹ አካላት በመረጃነት ከመጥቀሙም ባሻገር የህዝቡን ባህል፣ ወግና ልማድ ለተከታዩ ትውልድ በጽሑፍ ለማስተላለፍ ያግዛል፡፡

### 1.3 የጥናቱ ዘዴ

ከሚሰበሰቡ የመረጃዎች ዓይነቶችና መረጃዎቹን ለመተንተን ከሚያገለግሉ ዘዴዎች በመነሳት የምርምር ዓይነቶችን በሁለት መክፈል ይቻላል፡፡ እነዚህም ዓይነታዊ ምርምር (Qualitative Research) እና መጠናዊ ምርምር (Quntitative Research) ናቸው። የዓይነታዊ ምርምር ሂደት ተፈጥሮኣዊ ገፅታ ያለው ሲሆን፣ ምልከታ ማድረግ፣ ያዩትን መመዝገብ፣ የመዘገቡትን በተገቢ መንገድ መግለፅ፣ ያለውን ነገር እንዳለ ማሳየት የመሳሰሉትን ያካትታል (ያለው እንዳወቀ፡200118-20)፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ጥናት የመስክ ሥራ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል፡፡ ይህ የስም ስያሜ በዓል ጥናትም ዓይነታዊ ከሚባለው ሥር የሚመደብ ነው።

የጥናቱ የመረጃ ምንጮች የመጀመሪያ ደረጃ (ቀዳማይ) እና ሁለተኛ ደረጃ (ከልዓይ) ሲሆኑ የመጀመሪያ ደረጀ የመረጃ ምንጮች በመስክ ሥራ አማካይነት ስለሚጠናው ጉዳይ ከሚያውቁ ግለሰቦች ወይም ማህበረሰብ አባላት የሚገኙ ሲሆኑ፣ ሁለተኛ ደረጃ (ካልዓይ) መረጃዎች ደግሞ ከቤተመጻሕፍትና ከተለያዩ ዘገባዎች የሚወሰዱ ናቸው።

በዚሁ መሠረት ከቦረና ዞን ከያቤሎ ወረዳ የባህል እውቀት አላቸው ከተባሉት ሰዎች በታላሚ ናሙና ዘዴ አራቱን በቁልፍ መረጃ አቀባነት በመምረጥ እና በበኩር ስም ስያሜው በዓል ላይ ከተገኙት መካከል ንቁ ተሳትፎ የነበራቸውን ስለበዓሉ በመጠየቅና ምለከታ በማደረግ ቀዳማይ መረጃዎችን መሰብሰብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ስለ ስም ስያሜ አጠቃላይ ጽንሰ ሀሳብ

የሚያስገነዝቡ ካልዓይ መረጃ ጽሑፎች ከቤተመጻሕፍትና ከድህረገፆች ለጥናቱ እንዲውሉ ተደርገዋል፡፡

### 1.4 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

ፎክሎር የህዝቦችን ልማዶች፣ ወጎች፣ እምነቶችና ህዝባዊ ጥበቦችን ያካተተ ሰፊ የባህል ዘርፍ ነው፡፡ ይህንን የባህል ዘርፍ Dorson (1972:3-4) በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍለውታል[4]፡፡ እነርሱም፥ (1) *ሥነቃል* ፡- *ሥነቃል* በስሩ በርከት ያሉ በቃል የሚተረኩትን፣ የሚገጠሙትን፣ የሚዜሙትን ያጠቃልላል፡፡ (2) ቁሳዊ ባህል፡- ይህ የፎክሎር ዘርፍ ህዝቦች በራሳቸው ልምድና እውቀት በእጅ ያዘጋጁዋቸውንና የሚገለገሉባቸውን ቁሳቁሶች፣ የሚኖሩባቸውን ቤቶች፣ የሚለብሱዋቸውን አልባሳት፣ የሚመገቡዋቸውን ምግቦች፣ የሚጠጡዋቸውን መጠጦችና ሌሎች ቁሳዊ ነገሮች ይይዛል፡፡ (3) ሀገረሰባዊ ልማድ፡- በዚህ የፎክሎር ዘርፍ ስር ክብረ በዓላት፣ ፌስቲቫሎች፣ የሕይወት ዑደቶች የተለያዩ መንፈሳዊና ባህላዊ (አለማዊ) *ሥርዓቶች*[5] ይካተታሉ፡፡ (4) ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፡- በዚህኛው ክፍል ውስጥ ባህላዊ ሙዚቃዎች፣ ጭፈራዎች፣ ድራማዎች ይከወናሉ። የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ የሆነው የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ክዋኔዎች በባህሪያቸው ምክንያት በሀገረሰባዊ ልማድ ፎክሎር ክፍል ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ ህዝቦች እምነታቸውን፣ ማንነታቸውን፣ አንድነታቸውን የሚገልፁባቸውና በቤታቸው፣ በመንደራቸው፣ በእምነት ቦታዎቻቸው የሚያከብሩዋቸው የልደት፣ የስም ስያሜ፣ የጋብቻና የሞት ሥርዓቶች፣ የሚዘከሯቸው የተለያዩ የደረጃ ለውጦች፣ ዓመታዊና ወርሃዊ በዓላት የተለያዩ የፎክሎር ዘሮች ተደራርበው የሚከወኑበት ነው (Stephens and Sims 2005:95)፡፡ የሰው ልጅ ተወልዶ በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ እያለፈ እስከ እለተሞቱ የሚያደርጋቸው ሽግግሮች በበዓላት ይገለፃሉ (Gluckman,1962:2)፣(Gennep, 1960:3)፡፡ ለምሳሌ የክርስትና በዓል፣ የክርስትና ስም የሚሰየምበት ብቻ ሳይሆን ህፃኑ ወደ ክርስትና እምነት ተከታዮች መቀላቀሉን ከማብሰሩም በላይ የደረጃ ለውጡንም ያመለክታል፡፡ በባህላዊ ስም ስያሜም፣ ስም ያልነበረው ልጅ መጠሪያ ከሌለው የሚለይበትን የራሱ ስም ከማግኘቱ ባሻገር፣ በወጣለት ስምና

[4] የአራቱም ክፍሎች የአ"ማርኛ ትርጉም ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ካዘጋጁት የሥነ-ቃል መምሪያ የተወሰደ ነው፡፡

በተዘጋጀው በዓል ማብሰሪያነት ወደ ማህበረሰቡ መደመሩ የሚረጋገጥበት የማንነቱ መገለጫና የማህበረሰቡ ባህል ማሳያ መንገዶች አንዱ ሲሆን፤ ቤተሰቦቹንም፤ በየግላቸው ከሚጠሩበት ነጠላ ስማቸው፤ "የዕገሌ አባት፣ የእገሌ እናት" መባልን ያጎናፅፋቸዋል (Aregga, 2005:41) ፡፡
በኩር ልጅ አባትና እናቱ ሁለት ሆነው ጀምረው ወደ ቤተሰብ ማደጋቸውን፤ ዘር መቀጠላቸውን ያፈሩትንና ወደፊት የሚያፈሩትን ሀብትና ንብረት፤ ከወላጆቻቸው የወረሱትን፤ የትውልድ ታሪክና ባህል በቀጣይነት ማውረስ የመቻላቸው ማብሰሪያ ነው፡፡[6]

የስም ስያሜን ሥነሥረዓት የደረጃ ለውጥ ማህበረሰባዊ ባህርይ እንዲኖረው የሚያደርገው፤ ማህበረሰቡ በሰፊው የሚያከብረውና የሚሳተፍበት ሲሆን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በብዛት ተግባራዊ ሆኖ የሚታየው በወንድ የበኩር ልጅ የስም ስያሜ ጉዳይ ላይ ነው (Gennep 1960:62) ።

በአጠቃላይ ለፎክሎር ጥናት ዋና መነሻና መድረሻ የሆኑት የአውድና የክዋኔ ንድፈሀሳቦች ለዚህ ለቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስያሜ በዓል መተንተኛ ሆነው አገልግለዋል። Dorson (1972:46) እንደገለፁት አውድ ሲባል፡- ከዋኙ፣ ጊዜው፣ ቦታው፣ የአከዋወን ሁኔታውና ሂደት፣ የክዋኔው ታዳሚ፣ በከዋኙና ታዳሚው መሃከል ያለው ግንኙነትና ለክዋኔው መነሻ የሆነው ባህል ሁለንተናዊ ሁኔታ ይካተታል፡፡ በክዋኔ በኩልም በ Bauman (1977) ጥናት ውስጥ እንደቀረበው ከዋኙ፣ ታዳሚው፣ የሚከወነው የፎክሎር ዘርፍ፣ (ትረካ፣ ዝማሬ፣ የህይወት ዑደት በዓል፡- ልደት፣ ስም ስያሜ፣ ሠርግ፣ የቀብር ሥነሥርዓት) አከዋወንና የሚሰጡት ትርጓሜዎችና ሌሎችም ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ የክዋኔ ትንተና፣ ሕዝቦች ወይም ቡድኖች በባህላዊና በሌሎችም የፎክሎር ዘርፎች ክዋኔ ውስጥ መዋቅር እንዴት እንደሚዘረጉ፣ ሂደቶችን እንዴት እንደሚፈጥሩ፣ ክዋኔው ትርጉም እንዲኖረው እንዴት እንደሚሠሩ መመርመር እንደሆነም በዚሁ በ Bauman ጥናት ውስጥ ተገልጿል።

በዚህ የቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል (Gubbisaa) ክዋኔ ጥናት ላይም ይኸው የስም ስያሜው አውድ፣ የክዋኔ አፈፃፀምና በየክዋኔዎቹና አውዱ የቀረቡ የፎክሎር ዘሮች (genre) ለይቶ የመግለፅና የመተንተን ሥራ ተከናውኗል፡፡

---

[6] ጃተኒ ዲዳ ቃለመጠይቅ ፣ ሚያዝያ 26 ቀን 1999፣ ያቤሎ

## 2 የቦረና የስም ስያሜ ሥርዓትና የፎክሎር መከሰቻ አውድ

የቦረና ስም ስያሜ ሥርዓት ሁለት መልኮች አሉት፡፡ እነሱም Moggaasaa (ሞጋሳ) እና Gubbisaa (ጉቢሣ) ይባላሉ፡፡ ቀጥሎ ሁለቱ በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

### 2.1 Moggaasaa (ሞጋሳ)

የሞጋሳ ቀጥታ ትርጉሙ ስም ስያሜ ነው፡፡ በዚህ የስም ስያሜ ሥርዓት፤ ስም የሚወጣላቸው የቦረና ኦሮሞ ልጆች፣ ሴቶችና ታናናሽ ወንዶች ናቸው፡፡ አፈፃፀሙ ቀለል ያለ፣ ጥቂት ሰዎችን የሚያሳትፍ፣ ቤት ባፈራው ዝግጅት ብቻ በአንድ ቀን ውስጥ የሚጠነቀቅ ነው፡፡ የአሠያየሙ ሥርዓት ቀለል ያለ ቢሆንም አስፈላጊው ሥነሥርዓት ማሟላት የግድ ይሆናል። ቦርቦር ቡሌ ስለዚህ ጉዳይ ሲገልፁ የሚከተለውን ብለዋል፡

> Moggafni sagalee annan nyaatamu qofa dhiyeessuun baasan. Akki itti baasan garuu tokkuma, Guyyaan maqaaan itti Ayyaantuun murta'a, guyyaa dansa filtama, maqaan moggaafamu kan ijoolleeniifi maatiin isaanii lubbuun jiran sadii waliin walfakkaatu, maqaan galgala, moggaafama, abbaan horii kennaaf, namoonni jilicharratti argaman ni affeeramu, gmmachuu ta'a- የስም ስያሜው መከወኛ ቀን በ Ayyaantuu (አያንቱ) እንዲረጋገጥ ይደረጋል /ገዱ ጥሩ የሆነ ቀን ይመረጣል/፡ ፡ የሚሰየመው ስም በአካባቢው በሕይወት ያሉ ሦስት ልጆችና ወላጆቻቸውም በህይወት የሚገኙ ስም ጋር የተመሳሰለ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ የስም ስያሜው ሥነሥርዓትም ማታ ላይ ይከናወናል፡፡ አባት ለተሰያሚው /ለተሰያሚዋ/ ስጦታ ይሰጣል፡፡ በሥነሥርዓቱ ላይ የተገኙ ሁሉ የቀረበውን በልተው፣ ጠጥተው ጨፍረው ደስታቸውን ይገልፃሉ፡፡[7]

[7] ቦርቦር ቡሌ ቃለመጠይቅ ፣ሚያዝያ 24 ቀን 1999፣ ያቤሎ

### 2.2. Gubbisaa (ጉቢሣ)

ጉቢሣ ለታላቅ ወንድ ልጅ ስም ስያሜ በዓል የተሰጠ መጠሪያ ነው፡፡ ጉቢሣ በሁለት መልክ ሊታይ ይችላል፡፡ የመጀመሪያው የደበሌ ጉቢሣ (Gubbisaa-Dabballee) ሲሆን፤ ሁለተኛው የበኩር ልጅ ስም ስያሜ (Gubbisa- Angafaa) ነው፡፡[8]

#### 2.2.1. Gubbisaa-Dabballee (የደበሌ ጉቢሣ)

የደበሌ ጉቢሣ (Gubbisaa-Dabballee) በገዳ ሥርዓቱ ደበሌ በሚለው የዕድሜ ክልል (1-8) ሥር የታቀፉት ወደ ተከታዩ የዕድሜ ክልል "ጋሜ" (Gaammee) (9-16) ሲሸጋገሩ የሚከወነውን የስም ሥያሜ ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ የስም ስያሜ ሥርዓት፣ ስም የሚሰጣቸው በገዳ ሥርዓቱ በያአ (yaa'aa) ውስጥ የታቀፉ (የወቅቱ የገዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት) ደበሌዎች ናቸው።[9]

ቦርቦር ቡሌ እና ጃተኒ ዲዳ እንደገለፁት የገዳ ሥርዓቱ የየፓርቲዎቹ መሪዎች (አባገዳዎች) በስልጣን ዘመናቸው ከስምንቱ ዓመት ውስጥ ከሚከውኑት አንዱና ትልቁ ተግባር ተመርጠው አራት ዓመት እንደሰሩ፣ የአራቱን ዓመት የሥራ ክንውን ያስገመግማሉ፡፡ በዚህ በግምገማ ወቅት በሥልጣን ዘመኑ ከደበሌ ወደ ጋሜ ደረጃ ሊሸጋገሩ የተዘጋጁትን ደበሌዎች ይሰይማሉ፡፡ይህ የስያሜ ሥነሥርዓት በወላጆች ቤት የሚዘጋጅ አይደለም፡፡ በየስምንት ዓመቱ የሚከወን የየፓርቲው አንዱ ተግባር በመሆኑ፣ ነገሌ ከተማ አቅራቢያ ባለው "ኑራ" (Nuraa) በተባለ የገዳ በዓላት መከወኛ ቦታ ይፈፀማል፡፡ አንድ ቤተሰብ በስምንት ዓመቱ ውስጥ አከታትሎ ያፈራቸው ልጆች(ወንዶች) ካሉ ሁሉም ሊሰየሙ ይችላሉ፡፡ የስም ስያሜ በዓሉ ለነዚህ በየቤተሰቡ ላሉት ደበሌዎች ሁሉ በጋራ አንድ ጊዜ የሚከወን ይሆናልም ብለዋል፡፡

በመረጃ አቀባዮቹ ገለፃ መሠረት በማስከተል አባትና እናት ልጆቹን ይዘው ለስም ስያሜ ሥነሥርዓት አፈፃፀም ተዘጋጅተው ወደሚጠብቁዋቸው የኑራ አካባቢ አባ ገዳ ጋ ይሄዳሉ። እያንዳንዱ አባት ለልጁ እንዲወጣለት ቀደም ብሎ የመረጠውን ስም በመጥቀስ እንዲሰየምለት ይጠይቃል፡፡ ብዙውን ጊዜ በቤተሰብ የቀረበው ስም ይፀድቃል፡፡ ለደበሌ የሚወጣው ስም የአያቱ ስም ነው፡፡ ደበሌ በገዳ ህግ መሠረት የሚሰየም ስለሆነ እውቀት ያላቸው ስም ይሰየማል፡

[8] ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 26 ቀን 1999

[9] ቦርቦር ቡሌ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999

፡ በሥርዓቱ ለሚከወን ስም ስያሜ የበለጠ ቦታ ለመስጠትና ሰውም ሥርዓቱን እንዲያከብር ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አባገዳው የሚሰጠው ስያሜ አለ፡፡ ለምሳሌ ጀልዴሳ የሚል ስም ብዙውን ጊዜ የሚሰየመው በአባ ገዳው ነው፡፡ ጃልዴሳ የሚለው ስያሜ የሚሰጠው የደበሌዎችን የፀጉር አስተደደግ ለመግለፅ ፀጉራም ለማለት ነው ምክንያቱም ፀጉራቸው እንደ ዝንጀሮ ጎፈር እጅብ ያለ ስለሆነ በዝንጀሮ ይሰይሙዋቸዋል፡፡[10]

ይህ የሽግግር በዓል ካለፈ በኋላ በባህርይም ሆነ በቋንቋ አጠቃቀም ረገድ ለውጥ ይታያል፡፡ በዓሉ እስከሚከበርና ስም እስከሚወጣ ድረስ "አንቺ" እየተባለ የሚጠራው ደበሌ፣ አንተ ተብሎ መጠራት ይጀምራል፡፡ ከስም ስያሜ በፊት ደበሌ ልጆች በእናታቸው እንክብካቤ ስር ከመሆናቸው በተጨማሪ ከማህበረሰቡ በተለይ ከወንዶች ጎራ በስም ስያሜው ሥርዓት እስከሚቀላቀሉ በሴት ፆታ አንቺ ተብለው ይጠራሉ፡፡ አንተ ለመባል ስም መሰየም አለባቸው፡፡ አንድ ልጅ በሥርዓቱ ከተሰየመ በኋላ የቅፅል ስሙም አባገዳ ባፀደቀው አዲስ ስም ይተካል፡፡

### 2.2.2 የበኩር ልጅ ስያሜ (Gubbisaa Angafaa)

በቃለመጠይቅና በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ይህኛው ጉቢሳ ከሁለቱ የስም ስያሜ አይነቶች ይለያል፡፡ ጉቢሳ የቦረና ኦሮሞ የሆኑ ሁሉ ለመጀመሪያ ወንድ ልጅ ስም ስያሜ በቤታቸው የሚያዘጋጁት ትልቅ በዓል መጠሪያ ነው። በባህሉ ጂለ ጉቢሣ (Jila Gubbisaa) በመባል ይታወቃል፡፡ ("Jila") ትዕይንቶች የሚበዙበትና ብዙ ሰዎች የሚሳተፉበት ትልቅ ክብረ በዓል ነው፡፡ የአንድ ቤተሰብ ከታላቅ ልጅ ተከትለው የተወለዱ ታናናሽ ልጆች ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ቢኖሩት በዚሁ በጉቢሣ በዓል ላይ ሌላ ዝግጅት ሳያስፈልግ ይሰየማሉ (ni moggaafamu)፤ የበዓሉ ባለቤት ግን የበኩር ልጁ ነው፡፡

የበኩር ልጅ ስያሜ ጉቢሣ በዓል ታስቦበት ሰፋ ያለ ዝግጅት ተደርጎ የሚፈፀም በዓል ነው። በመሆኑም የጉቢሣ በዓል የሚያዘጋጅ ቤተሰብ (Warra jilaa) የበዓሉን መከወኛ ጊዜ ጠቅሶ ወገኑንና ጎሣውን "የታላቅ ልጃችን የስም ስያሜ በዓል የሚከወንበት በዚህ ቀን ስለሆነ እንድትገኙልን" ብሎ ከመጥራቱ አስቀድሞ ለበዓሉ የሚስማማውን ጊዜ /ቀን/ /ጥሩ ገድ የሆነ/ ለይቶ ለመወሰን እራሱ ካላወቀ ወደ Ayyaantyuu[11] (አያንቱ) ይሄዳል፡፡ አያንቱዎች ጥሩና መጥፎ ገድ የሚውልበትን ቀን ለይተው የማወቅ ችሎታ አላቸው ስለሚባል የጉቢሣው በዓል ቀን ጥሩ ገድ ያለው ቀን እንዲነግሩዋቸው ይጠይቃሉ፡፡ አያንቱዎችም ኮከብ ቆጥረው በወር ውስጥ ካሉት ሃያ ሰባት በዓላት መካከል "ቢታ" (Bitaa) "ጊዳዳ" (Gidaadaa) የተባሉ በዓላት ባልዋሉባቸው ቀናት ውስጥ የስያሜ በዓሉን እንዲከውኑ ይናገራሉ፡፡ በቦረና ቀን አቆጣጠር በወር ውስጥ ሃያ ሰባት በተለያየ ስም የሚጠሩ በዓላት አሉ፡፡ ከእነዚህ ቀናት መካከል"ቢታ" (Bitaa)

---

10 መረጃ አቀባዮቹ በቃለመጠይቅ ጊዜ እንደ ገለፁት

11 አያንቱ ልዩ መንፈሳዊ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ "Asaastuu Waaqaa" ተብለውም ይታወቃሉ፡፡ ይህ ማለት ከፈጣሪ ወይም ከአምላክ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የሚታመንባቸው ናቸው፡፡

እና "ጊዳዳ" (Gidaadaa) የተባሉት በዓል ለማክበር ይከብዳሉ፣ ለባለጉዳዩ (ለተሰያሚው) የወደፊት ህይወት አይበጁም ሙሉ አይደሉም ስለሚባሉ አይመረጡም፡፡[12]

የጉቢሣ በዓል የልጁ ወላጆች የግል ጉዳይ አይደለም፡፡ የወገኑ፣ የጎሣው ሁሉ ጉዳይ ነው፡፡ "Gubbifni dirqma. Namni ilma gubbifachuuf horii dhabellee gosti seera ittiin walgargaaru waan qabuuf horiin bahee ni gubbisa. Boorana ta'ee kan hin gubbifne seera cabse Jedhamee waan gosaaf godhan hin godhaniif garuu yakka qaba hin jedhan gosa Keessaa baha malee - ጉቢሳ በዓል ማዘጋጀት ግድ ነው፡፡ እነዚህ የታላቅ ወንድ ልጅ ወላጆች፣ ለበዓሉ ዝግጅት አቅም የሚያንሳቸው ቢሆን እንኳ ከዘመዶቻቸው ባሻገር የጎሣ አባል የሆኑ ሁሉ እገዛ አድርገው በዓሉ አስፈላጊ በሆነ አኳኋን እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡ በበዓሉ ልጅ አለማሰየም ወንጀል ነው ባይባልም ከማህበረሰቡ እንዲገለሉ ያደርጋል"[13]። ስም ያልተሰየመ ልጅ በአጋጣሚ ቢሞት እንኳ ቀብሩ የሚፈፀመው በመኖሪያ ቤት ውስጥ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከማህበረሰቡ ጋር አልተቀላቀለም ወይም ሙሉ ሰው አልሆነም ማለት ነው፡፡

በጉቢሣ ስም ስያሜ ሥርዓት የቀን አወሳሰን ላይ መታየት ያለበት ጉዳይ የወላጅ አባት የእድሜ ሁኔታ አለ። ይኸውም የገዳ ሥርዓቱ በሚፈቅደው የጊዜ ቀመር ውስጥ አግብተው የወለዱ "እልማን ኮርማ" ይባላሉ። ጥሬ ትርጉሙ የኮርማ ልጅ ማለት ነው፡፡ኮርማ በሮሞ ቋንቋ ጀግና፣ ጎበዝ የሚል ፍች አለው፡፡ ባጠቃላይ የገዳ ስርዓቱን የጠበቀ ወንድ ልጅ ማለት ነው፡፡ እንዲህ ያሉ እልማን ኮርማ የሚባሉት በሙሉ የስም ስያሜያቸው በተመሳሳይ ጊዜና ቀን የሚወሰን ይሆናል። በግለሰቡ ደረጃ ሊወሰን የሚችለው ዓመቱን መምረጥ ብቻ ነው፡፡ በዚህኛው ዓመት ያልሞላለት በተከታዩ ዓመት ሥርዓቱ በሚፈቅደው ጊዜ እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡

በጃተኒ ዲዳ ገለፃ መሠረት በገዳ ሥርዓቱ የጊዜ ቀመር አግብተው መውለድ ሲገባቸው ዘግይተው ያገቡና ያፈሩዋቸው ልጆች ደግሞ እልማን ጃርሣ የሚባሉ ሲሆኑ፣ ልጆቻቸው ከአንድ ዓመት በላይ ዕድሜ ማስቆጠር ሲጀምሩ ስም ለማሰየም የተመቻቸውን ጊዜ መርጠው፣ ጥሩ ገድ ያለውን ቀን በአያንቱ አስቆጥረው ዘመዶቻቸውንና የጎሣ አባሎቻቸውን ጠርተው ያከብራሉ፡፡ በእልማን ኮርማና በእልማን ጃርሣ የጉቢሣ በዓል አከባበር መሀከል ያለው ልዩነት በዓሉ

[12] ጃተኒ ዲዳ ቃለ መጠይቅ ሚያዚያ 26 ቀን 1999

[13] ቦርቦር ቡሌ ቃለ መጠይቅ ሚያዚያ 24 ቀን 1999 ፡፡

የሚወስደው ጊዜ ብቻ ነው፡፡ይኸውም፣ የእልማን ኮርማ ልጆች የጉቢሳ በዓል መሰየሚያ አዳራሽ (Galma) ሥራ በሁለት ቀን ውስጥ የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡ የእልማን ጃርሳ ደግሞ የአዳራሽ ሥራ በአንድ ቀን ተጠናቆ በዕለቱ ሊሰየምበት ይችላል ማለት ነው።በቦረና ባህል ባህላዊ ሥርዓት የሚከወኑት በገልማ ውስጥ ነው፡፡ገልማ አዳረሽ ማለት ነው፡፡ በመጣኑ ትልቅም ትንሽም ሊሆን ይችላል፡፡ ክብደት የሚሠጠው ሥርዓት በውስጡ መከወኑ ነው፡፡

የቀናቱ ስፋትና ጥበት የድርጊቶችን መብዛትና ማነስ አያመለክቱም፡፡ የቀናቱ ልዩነት፤ በገዳ ሥርዓቱ የጊዜ ቀመር መሰረት ተወልደው ለበዓሉ ለደረሱት ክብርና ክብደት ለመስጠት ለአዳራሹ ሥራ ሁለት ቀን እንድሆን ተደረገ እንጂ፤ የአዳራሹ ሥራ ክብደትና ውስብስብነት ከአንድ ወደ ሁለት ቀናት ቆይታ አላሳደጉትም፡፡[14]

ቦረቦር ቡሌ አንደ ገለፁት ለጉብሣ በዓል ዝግጅት እናትና አባት የየራሳቸው የሆነ የሥራ ድርሻ አላቸው፡፡ በቦረና ኦሮሞ የሥራ ክፍፍል መሰረት፣ በቤት ውስጥ የሚከወነውና የመኖሪያ ቤት ግንባታ በሴቷ ትከሻ ላይ የወደቀ ጉዳይ ነው፡፡ በውጭ የሚሠሩ የበዓላት ጉዳይ (jila tolchuu)፣ የአካባቢውን ሰላም መጠበቅ (ወታደራዊ ሥራ)፣ ከብቶች ሣርና ውሃ ወዳለበት እሩቅ ቦታ ማሠማራት፣ ከጥልቅ ጉድጓድ ለከበቶች ውሃ ማምጣትና ማጠጣት የወንዱ ድርሻ ነው።

በዚሁ የሥራ ድርሻ መሰረት ለበዓሉ የልጁ እናት ከቆዳ የሚሰራ "ከሎ" (Kaloo)[15] ታዘጋጃለች። ከሎ ለጉቢሣ በዓል አስፈላጊና ዋንኛ አልባሳት ከሚባሉት መሀከል አንዱ ነው፡፡ ለማዘጋጀት ከቆዳ በተጨማሪ ዛጎል ያስፈልጋል፡፡ ዛጎሉ ደግሞ በገዳ ሥርዓቱ በስልጣን ላይ ያሉ ቤተሰቦች ከሆኑ ከደበሌ ወደ ጋሜ ሽግግር ሲደረግና ፀጉር ሲላጭ ተለቅሞ ከሚቀመጠው አንጂ ተገዝቶ ከሚቀርበው አይዘጋጅም፡፡[16]

ይህን በዛጎል ያጌጠ ከሎ የሚለብሱት የልጁ እናት፣ አባትና ሴት አያቶቹ ናቸው፡፡ ለበዓሉ ቢያንስ አምስት ከሎች ያስፈልጋሉ፡፡ እናት አንድ፣ ሁለቱ ሴት አያቶችም አንዳንድ፣ አባትየው ሁለት ከሎዎች ይለብሳሉ። ይህ ከሎ ልክ አንቀልባ የሚመስል ስለሆነ አባትየው ሁለት ሲለብስ ማዘያ ያስመስለዋል፡፡

---

[14] (ቦርቦር ቡሌ፤ ቃለ ምልልስ ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.)

[15] ከሎ ከተለሰለሰ የፊየል ቆዳ የሚዘጋጅ በልብስ ላይ ከወገብ በላይ የሚደረብ በዛጎልና የተለያዩ ማጌጫ ቁሳቁሶች ያማረ ባህላዊ ቁሳቁስ ነው

[16] ጃተኒ ዲዳ ፤ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 26 ቀን 1999 ዓ.ም

ስም የሚያስይመው አባት እልማን ጃርሳ ከሆኑ ደግሞ፣ ቀደም ብሎ ከሎ አዘጋጅተው ልጃቸውን ከሰየሙ ቤተሰቦች ይዋሳሉ፡፡ ሲዋሱ እንዲሁ በደረቁ አውሱኝ ብለው አይጠይቁም፡፡ "ደራራ ተንቦ" እጅ መንሻ፣ መማፀኛ ይዘው ነው፡፡ ይህ ደራራ የሚባለው ቡና፣ ወተት፣ትንባሆ፣ ሰርዶን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ ቁሶች የፈጣሪ፣ እንዲሁም በባህሉ ክብር የሚሰጣቸው ሰዎች መማፀኛ(መለማመኛ) ናቸው፡፡[17] ሌላው እናትየው የምታዘጋጀው ለበዓሉ ተሳታፊዎቸ ማስተናገጃ የሚውል ቅቤ፣ ቡና፣ ማጣፈጫዎችን እንዲሁም የምግብና መጠጥ ዝግጅት ዕቅድ ይሆናል፡፡

በአባትየው በኩል የሚደረገው ዝግጅት፣ በእናትየው የቀረበውን ዕቅድ መርምሮ ካሉት ከብቶች ውስጥ ሊሸጡ የሚችሉትን መርጦ፣ ለበዓሉ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በተለይ ለምግብና መጠጥ ማዘጋጃ የሚውሉትን መግዛት ነው፡፡ ከዚህ በዓል ዝግጅት ውስጥ መቅረት የማይችሉ እንደ "ደራራ ተንቦ" ያሉት በዚህ ግዢ ውስጥ ይጠቃለላሉ፡፡[18]

#### 2.2.2.1 የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል አውድ

ለዚህ ጥናት በአካል ተገኝቼ የተመለከትኩትና ሙሉ የበዓል ክዋኔ መረጃዎች የሰበሰብኩት በቦረና ዞን በያቤሎ ወረዳ ከተከበሩት የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓላት ከያቤሎ ከተማ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሰላሳ ኪሎ ሜትር ርቆ ከሚገኝ ዳዲ (Dhaddii) ከተባለ የገጠር ቀበሌ የአባሩፋ ጃተኒ ልጅ ስም ስያሜ በዓል ነው፡፡የዚህ ነዑስ ክፍልና በስሩ የቀረቡት የስም ስያሜ ክዋኔ መረጃዎች በሙሉ በምልከታ እና አውዱ ላይ ከነበሩት ሰዎች በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡

አብ[19] አባሩፋ ጃተኒ የቦረና ተወላጅ፣ የሰቦ ጎሳ አባልና የአንድ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ባልደረባ ናቸው፡፡ወደ ደዲ መንደር የተጓዙት የልጃቸውን የስም ስያሜ በዓል ጉቢሣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር፣ በትውልድ መንደራቸው ለማክበር ነው፡፡ ለበዓሉ ታዳሚ የከተማ ነዋሪዎች ድንኳን አዘጋጅተዋል፤በዓሉን ለመቅረፅም ሆነ የደመቀ ለማድረግ ጀኔሬተር ተከለዋል፡፡

[17] (ካሉ ጂሎ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም.፡፡

[18] ቦርቦር ቡሌ፣ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም

[19] አብ የሚለው ቅፅል ቦረናዎች ከወንዶች ስም ጋር አቶ ለማለት የሚጠቀሙት ስለሆነ እኔም በዚህ ጥናት ውስጥ አልፎ አልፎ ተጠቅሜያለሁ

በዚህ በበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓሉ የሦስት ቀን ቆይታ ውስጥ በዋዜማውና በየዕለቱ የተለያዩ ክዋኔዎች ተስተናግደዋል፡፡ በአብ አባሩፋ ቤት የዋዜማው ዕለት ሁለት ሰዎች ሀዩ(Hayyuu) የተባሉ በማህበረሰቡ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ተመርጠው የእንጨት ሁሉ ታላቅ የተባለ፣ የወዴሣ (Waddeessaa) ሁለት እንጨት ቆርጠው አመጡ፡፡ እነዚህ ሰዎች እንደወትሮው ውሎአቸው አለባበስ ሳይሆን ለበዓል ቀን የሚያስፈልገውን አለባበስ አሟልተው ነው የተገኙት፡፡ በራሳቸው ላይ የቦረና መለያ ምልክት የሆነውን ሱሬ ሩፋ (Surree Ruffaa) ጠምጥመው፣ በእጃቸው ሆሮሮ (Horooroo) የአባገዳ በትር አይነት፣ ከአውራሪስ ወይም ከቀጭኔ ቆዳ የሚዘጋጅ መግረፊያ መሰል፣ ሊቾ (Lichoo) ይዘው፣ እንጨቱ ወደሚገኝበት ቦታ አመሩ፡፡ ከሆሮሮ በስተቀር ዱላ ወይም ጦር አይያዝም፡፡ ይህ የሚያመለክተው ማንንም የማይነኩ ሰላማዊ መሆናቸውን፣ እንዲሁም ሌላው አካል ይህን ተገንዝቦ እንዳይተናኮላቸው ማሳወቂያ ዘዴ ነው፡፡ [20] ሀዩዎቹ ቆርጠው ያመጡትን ወዴሣ (Waddeessaa) ከበዓል መከበሪያው ደጃፍ የከብቶች በረት ምልክት ከሆነው ቡቱሜ (Butume) ኋላ አስቀመጡት፡፡

በዚሁ በዋዜማ ዕለት በበዓሉ መከበሪያ መንደርና አካባቢው ካሉት ከቦረና አባላት መካከል ቶርበን ጅላ (Torban jilaa) የተባሉትም ተመረጡ፡፡ ቶርበን ጂላ የበዓሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን የያዘ ነው፡፡

በዚህ በቶርበን ጅላ አወቃቀር ውስጥ የቦረና ሁለቱ ትላልቅ ክፍሎች ስብጥር ጎልቶ ይታያል፡፡ ይኸውም የጉቢሣ በዓል የተዘጋጀለት ልጅ አባት አባ ሩፋ ጃተኒ የሰቦ አባል ናቸው፡፡ የቶርበን ጅላው አባላት አባትየውን ጨምሮ፣ አራቱ የሰቦ አባላት ሲሆኑ፣ የተቀሩት ሦስቱ ደግሞ የጎና ጎሣ አባላት እዲሆኑ ተደርገ፡፡ እነዚህም አባላት ሲመረጡ ታላቅ ታናሽነታቸውን ለመለየት የየትኛው ንዑስ ጎሳ አባል እንደሆኑ እየተጠየቁ የታላቅ ጎሳ አባል ለሆኑ ቅድሚያ እየሰጡ መረጡዋቸው፡፡ ለምሳሌ ከሰቦ ንዑሳን ጎሳች ድገሉ ከጎና ደግሞ ፉላሌ ታላቅ ናቸው፡፡›

ከነዚህ ከሰባቱ የበዓሉ አስፈፃሚ አባላት አንዱ ቀደዱ (Qadadduu) ተብሎ ተመረጠ፡፡ ቀደዱ የበዓሉ ሥነሥርዓት መሪ ነው፡፡ ቀደዱ ከሁለት ዋና ዋና የቦረና ክፍሎች የአንዱ አባል መሆን ይችላል፡፡ ቀደዱን ለመምረጥ የሚያስፈልገው መስፈርት፣ ተመራጩ በገዳ ሥርዓቱ በሉባ (Luba) ደረጃ ውስጥ ያለፈ መሆን ነው፡፡ ሉባ ማለት አባገዳ ለመሆን የሚያስችሉት ሂደቶችና

[20] (ካሉ ጂሎ፣ ቃለ መጠይቅ ሰኔ 12 ቀን 1999፣ ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 22 ቀን 1999)፡

ደረጃዎች ያጠናቀቀ ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በዋዜማው ዕለት ቶርበን ጅላዎቹና ቀደዱው ማን እንደሆኑ ተለይቶ ታወቀ፡፡

**2.2.2.1.1 "ሙከሙራ"(Muka Muraa) የመጀመሪያው ዕለት**

የሙከሙራ ቀጥታ አማርኛ ትርጉሙ እንጨት ቆረጣ የሚል ነው፡፡ በዚህ በመጀመሪያው ዕለት ጥሪ የተደረገላቸው ከሩቅ የሚመጡ ቤተዘመዶች፣ የጎሣ አባላትና ጓደኞቻቸው አብዛኛው ተገኝተዋል ማለት ይቻላል፡፡ መመልከት እንደተቻለው ሙሉቀን ሰው ሳይቋረጥ ሲመጣና ሲስተናድ ውሏል፡፡

በዚህ ዕለት፣ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት አከባቢ የበዓሉ ባለጉዳዮች፣ እናት፣ አባት፣ የልጁ የሴት አያቶችና ልጁ ከወትሮ የተለየ ልብስ ለብሰው ወጡ፡፡ ሴቶች ከሥር "Gorfoo" ጎርፎ (ከቆዳ የተሰራ ቀሚስ) ከላይ ለጉቢሣ በዓል የተዘጋጀውን "ከሎ" ደርበዋል፡፡ በእጅ ሲቄ (ቀጭን በትር) ይዘዋል፡፡ አባት (Abbaa jilaa) ደግሞ ከታች ሸርጥ ከላይ ሴቶች እንደለበሱት አይነት ሁለት ከሎ ለብሰዋል፣ በእጃቸው፣ ዳኒሣ በትር እና ሊቾ ይዘዋል፡፡ እራሳቸው ላይ ሱሬ ሩፋ ጠምጥመዋል፡፡ሱሬ ሩፋ በራስራይ የሚጠመጠም ከተለያየ ቀለም በሸመና የሚሠራ ነው፡፡ አባሩፋ ከበኩር ልጃቸው በተጨማሪ ታናሹንም በዚሁ በዓል ላይ በሞጋሣ ሥርዓት ለማሰየም ይዘው ስለቀረቡ ለሁለቱም ልጆች አንድ አይነት አዳዲስ ልብስ አልብሰዋቸዋል፡፡

እንዲህ ባለ ሁኔታ የባህልና የበዓል ልብስ ለብሰው ካቀረቡ በኋላ የበዓል አዘጋጅ እናት (Haddha Jilaa) ወ/ሮ ከሹ አባሩፋ አነስ ያለ ቁርበት ይዛ ከፊት እየመራች ከከብቶች በረት ገባች፡፡ ከኋላ ደግሞ ሌሎች ሴቶችና የአባጅላው እናት ተከትለው የለሰለሰ ቁርበት ይዘው በትንሽ ቢላዋ መሰነጣጠቅ ጀመሩ፡፡ ይህን ሰነጣጥቀው በክብ ቀደው ያወጡትን በልጁ እናት በወ/ሮ ከሹ አባሩፋ እጅ ላይ አጠለቁላት፡፡ ይህን የወግ ቁስ (Saqaa) ስቃ ይሉታለ፡፡ የታላቅ ወንድ ልጅ እናት መሆኗ የሚገለፅበት ነው። ተተልትለው በተንጠለጠሉት ጫፎች ላይ ዶቃና የተለያዩ ድምፅ የሚሠጡ ማጌጫዎችም ሰካኩበት፡፡ ያንን ተሰንጣጥቆ በእጇ ልክ የተዘጋጀውን ቆዳ አጥልቃ አስቀድማ ይዛ በቀረበችው ቁርበት ላይ፣ ከበረት አዛባ በቀኝ በኩል ያለውን አንስታ በበረቱ መውጫ በቀኝ በኩል በረቱ ውስጥ እንደ መከመር ሞለል አድርጋ ተወች፡፡

ከበረቱ በግራ በኩል ባለው አካባቢም እንዲሁ አነሳስታ ከበረቱ ውጭ የከብት በረት ምልክት ነው ከሚባለው ከቡቱሜ (Butumee) እንጨት በኋላ ሞለል አድርጋ እንደመከመር አደረገች፡፡

ከሁሉ ሥራ በፊት አዛባ ማንሳቱ አካባቢ ማፅዳት መቅደሙን ለማመልከት ነው፡፡ ከብቶች ከበረት ሲወጡ እንዳይረጋግጡ ቀድሞ ማንሳት ስለሚያስፈልግ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ወደ ቤት ተመልሰው "ቡነቀላ" አዘጋጅተው፣ተመረቁ፡፡ ቡነቀላ ቀጥታ ትርጉሙ ቡና እርድ ማለት ነው፡፡ አሠራሩ፣ ቡና ድፍኑ ጫፍ ጫፉ ተቆርጦ በማሰሮ ወይም ብረት ድስት ውስጥ ተጨምሮ በተነጠረ ቅቤ እስከሚንጣጣ ድረስ ይጠበሳል፡፡ ትኩስ ወተት ተጨምሮበት ለምርቃት ይቀርባል፡፡ ይህ ነው ቡነቀላ ማለት፡፡ በባህሉ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው የሥርዓት መከወኛ ነው፡፡

በዚህ በስም ስያሜ በዓል ላይ ቡነቀላውን ያዘጋጁት የአባሩፉ ባለቤት የቅርብ ዘመድ የሆኑ ወ/ሮ ሲሆኑ ምረቃውን የሰጡት በሀዩ ደረጃ ያሉ ሽማግሌ ናቸው፡፡ ምረቃው በጣም ረዥም ነው፡፡

| | |
|---|---|
| Bobba'an nagayaa | - የሚሰማራ ሰላም |
| Bobbaan nagayaa | - ስምሪት ሰላም |
| Oolmaan nagayaa | - ውሎ ሰላም |
| Galchuun nagayaa | - መመለስ ሰላም |

እያለ የዕለቱን እንቅስቃሴ ከመመረቅ ጀምሮ፣ ህዝቡን፣ ሥርዓቱን፣አካባቢው ሰላም እንዲሆን የሚመኝ ሀሳብ እያቀረቡ ጉዳዩ እየሰፋ ይሄዳል፡፡ ቡነቀላው ተመርቆ ከቀረበ በኋላ ሁሉም ቀምሳው፣ የልጁ እናት መጥረቢያ ይዛ ሌሎች ሴቶችን እየመራች "ሀንደራካ (Handaraaka)" የተባለ እንጨት ቆረጣ ሔዱ፡፡ እንጨቱን መጀመሪያ እራሷ ቆርጣ፣ ለሴቶች ቅርንጫፎቹን ከፋፍላ እርሷ እየመራች፣ ወዴሣ እንጨት ተቆርጦ የተቀመጠበት ቦታ ላይ አሳረፉ፡፡ ይህ ሀንዳራካ የተባለ እንጨት ከወዴሣ ቀጥሎ የሚቆረጥ ለበዓሉ አዳራሽ (ገልማ) መሥሪያ እንደ መሠረት መጣያ የሚወስድ ነው፡፡[21]

ሴቶቹ ሀንዳራካውን ቆርጠው አምጥተው ካስቀመጡ በኋላ ካርሌ (kaarlee) የሚባል ዘፈን ዘፈኑ፡፡ ቁጥራቸው አነስተኛ ስለነበር አልደመቀላቸውም፡፡ ለትንሽ ደቂቃ ወጉን አድርሰው አቆሙ፡፡ የዘፈኑ ይዘት ባለጉዳዩቹን በተለይ አባትየውን የሚያሞግስ ነበር፡፡

በዚህ እንጨት ቆረጣ ዕለት (muka muraa) ከሰባት ሰዓት በኋላ ጀምሮ ብዙ ሰዎች ከየአቅጣጫው፣ ወጣት፣ አዋቂ ሳይቀር ለገልማ ሥራ የሚውል እንጨት ቆርጠው ወደበዓሉ ቦታ

[21] (ጃተኒ ዲዳ፣ቃለ መጠይቅ ፣ሰኔ 14 ቀን 1999)

ሲያጓጉዙ ዋሉ፡፡ ወንዶች፣ ትላልቅ ለቋሚ የሚሆን እንጨት፣ ሴቶች ደግሞ ቀጫጭን ለማገርና ለሣጋ የሚሆነውንና በገልማው ግድግዳና ጣራ እንዲለብስ የሚደረገውን ሣር ቆርጠው፣ አጭደው አመጡ፡፡ እዚህ ላይ በቦረናዎች ዘንድ ለበዓል ሆነ መደበኛ ቤት ለመስራት የሚውለው እንጨት እንደ ተገኘ አይቆረጥም፡፡ ሊቀጥል የሚችል ቅርንጫፍ ታይቶ ይቆረጣል እንጂ ግንዱ አይነካም፡፡

ለገልማው መሥሪያ የተቆረጠውም እንጨት፣ ሣሩም እንደ ወዴሣውና ሀንደራካው ከበረቱ ደጃፍ ተከምሮ አደረ፡፡ ይህ ዓይነቱ የቤት ሥራ ላይ ትብብር፣ ጉዳዩ በዓል ሰለሆነ እንጂ ለወትሮ ቤት ሲሠራ እንጨት ቆርጠው የሚሠሩት ሴቶች ብቻ ናቸው፡፡

እንጨትና ሣሩን ሲያጓጉዙ የዋሉትንና በእንግድነት ከሩቅ ተጠርተው የመጡት ሁሉ ወደ ቤት ገብተው እንዲስተናገዱ ተደረገ፡፡ በመስተንግዶው መጀመሪያ በበዓሉ ቤት ውስጥ ለተሰበሰቡት እንግዶች፣ አባትየው ወይም የጉዳዩ ባለቤት (Abbaa jilaa) ትንባሆና ለምለም ቅጠል በበዓሉ ላይ ለተገኙ ሁሉ "እነሆ ለምለም" (Hoodhaa! daraaraa) ብሎ ሰጣቸው፡፡ እነርሱም፣ "Saawwaafi namaan daraari" በሰው በከብት ለምልም ብለው ተቀበሉ፡፡ ይህ ድርጊት በውስጡ እንኳን ደኅና መጣችሁ፣ ይህን በዓል መርቁልኝ የሚል መልዕክት ይዟል፡፡ የታዳሚዎቹም ምላሽ መሰረታዊ የሆነ ምርቃት ነው፡፡ ሀብትና ልጅ አብሮ ይስጥህ ማለት ነው፡፡

በመቀጠል ወተትና ውሃ ተቀላቅሎ ለውሃ ጥም ተሰጣቸው በቦረናዎች ውሃ ባዶውን መጠጣት እጦት፣ ድርቅ አመልካች ነው፡፡ ውሃ ወተቱ ላይ የሚቀላቀለው ጥም እንዲቆርጥ ነው፡፡ ከሥጋና ከበቆሎ የተዘጋጀ ንፍሮ የመሰለ ምግብ በትላልቅ ጎድጓዳ ፕላስቲክ ሳህን በቡድን በቡድን ቀርቦላቸው በሉ፡፡ ቡነቀላም ተዘጋጅቶ ተከፋፈለ፡፡እስከ በዓሉ ማጠናቀቂያ ቀን ለመቆየት ብለው ከመጡት የሩቅ አካባቢ እንግዶች በቀር ሌሎቹ የዕለቱን ሥራ በዚሁ አጠናቀው ወደየቤታቸው ተመለሱ፡፡ የበዓሉ ባለቤቶች እናትና አባት ሳይቋረጥ የሚመጡትን እንግዶች እየተቀበሉ፣ ይዘው የሚያመጡትን ጉማተ(gumata)(ስጦታ) እየተረከቡ ሲያስተናግዱ ዋሉ፡፡ ለሚያድሩትም አስፈላጊው መስተንግዶ እንዲደረግ ላስቀመጡዋቸው አስተናጋጆች እየነገሩ፣ ሰው በተገቢው መንገድ ሲስተናገድ አመሸ፡፡ ለምግብ ፍየልና በሬ ታርዶ ተዘጋጀ፤ ወተት፣ጠጅና

አረቄም በመጠጥነት ቀረቡ።ቡነቀላ የማያቋርጥ የመስተንግዶው ነበር። በቦረና ቡና በቡነቀላ እነጂ፣ ተቆልቶ፣ተወቅጦ ተፈልቶ አይቀርብም ፡፡[22]

#### 2.2.2.1.2 "የየባ" (Yayyabaa) የበዓሉ ሁለተኛው ቀን

በዚህ ቀን ከሚሠሩ ሥራዎች መሀከል ትልቁ፣ የህፃኑ ስም የሚሰየምበትን የበዓል ዳስ "ገልማ" (Galma) መሥራት መጀመር ነው፡፡ የስም ስያሜው በዓል የእልማን ኮርማ ከሆነ የገልማው ስራ ይጀመራል እንጂ በዕለቱ አይጠናቀቅም፡፡ ማጠናቀቅ ቢቻልም እንዲያድር ይደረጋል፡፡ ይህ ሁሉ በዓሉ ትልቅ በዓል ስለሆነ ለበዓሉ ለሚሠራው ገልማም ክብደት ለመስጠት ነው፡፡[23]

በዚህ በሁለተኛው ቀንም እንደ እንጨት ቆረጣው ዕለት ከጠዋቱ አንድ ሰዓት አካባቢ፣ ከብቶች ከበረት ሳይወጡ፣ የልጅ እናት፣ በወጉ ለብሳ ከታች ጎርፎ፣ከላይ ከሎ፣በእጇ ሲንቄ ይዛ፣ሰቃ በቀኝ እጇ አጥልቃ፣ አነስተኛ ቁርበት ይዛ ከኋላዋ ጥቂት ሴቶች እየተከተሉ ከበረቱ ገባች፡፡ በበረቱ ውስጥ በቀኝ በኩል ያለውን አዛባ በቁርበቱ ላይ አንስታ በቀኝ ከበረቱ መውጫ የመጀመሪያ ዕለት ሞለል አድርጋ በመጀመሪያው ቀን ከከመረችው ላይ ጨመረች፡፡ በግራ በኩል ያለውንም እንደዚው አነሳስታ ከበረቱ ውጭ ከተቀመጠው ቡቱሜ ጋ ከተከመረው ላይ ጨመረች፡፡

ከበረቱ ከተመለሰች በኋላ፣ ለገልማው እንደመሠረት መጣል የሚቆጠረውን የሀንዳራካ እንጨት በገልማው መሥሪያ ቦታ ላይ ከአማቷ ጋር አኖሩ፡፡ አቀማመጡም ከገልማው በር ትይዩ "ቦሮ" ላይ ነው፡፡

ቀጥሎ የተከወነው የገልማውን ሥራ ማስጀመር ነው፡፡ የጉቢሣ ሥነሥርዓት  የሚፈፀምበትን ገልማ ሥራ የእንጨት መትከያ ጉድጓድ ቆፍሮ ያስጀመረው  "ቀዳዱ" ተብሎ የተመረጠው ሰው ነው፡፡ ከቀዳዱ በፊት ማንም መጀመር ወይም ማስጀመር አይችልም፡፡ ቀደዱ መሪ ማለት ነው፡፡ ከገዳ ሥርዓቱ ተሳታፊ ሀዩዎች( ምሁራን/አወቂዎች) የሚመረጥ ነው፡፡ የበዓሉ ባለቤት(Abbaa jilaa) ምሳሩን መሰንዘር የሚችለው ከቀደዱ ቀጥሎ ነው፡፡ ለዚህም ነው አባሩፉ ቀደዱው መሬቱን ቆፍሮ እንጨቱን ተክሎ ለማጥበቅ ከላይ ሲመታ ያዙለት እንጂ ቀድመው ምንም አላደረጉም፡፡

---

[22]ኑራ ጉዩ፣ቃለመጠይቅ፣ሰኔ 14 ቀን1999

[23] ካሉ ጂሎ፣ ቃለመጠይቅ ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም.

ቀደዱው ይህን የገልማውን ሥራ ሲጀምር "mucaan siif haa bulu, haaguddatu" (ልጅህ ይኑርልህ ይደግልህ) ብሎ የመሥሪያ እንጨቱን ልክ "ሀንዳራካው"እንጨት የተቀመጠበት ላይ ነው የተከለው፡፡ አባትየውም ከዚያ ቀጥሎ ሌላ ቋሚ እንጨት ተከለ፡፡ ከዚያ በኋላ ሌሎች የበዓሉ ተሳታፊ ወንወዶች ዙሪያውን ቋሚ በማቆም የገልማውን ሥራ ማገዝ ጀመሩ፡፡ በባህሉ ቤት መሥራት የሴቶች ድርሻ ስለሆነ ከቋሚ ተከላና ዋና ማገር በኋላ ሙሉ በሙሉ ተረክበው መሥራት ጀመሩ፡፡ እናትየዋና አያቱ በጓሮ የበሩ ትይዩ ሀንዳራካ እንጨት ከተቀመጠበት ቦታ ጀምረው ሳጋ መጠቅጠቅ ጀመሩ፣ ሌሎችም ተከተሉዋቸው፡፡ ወንዶች ማሰሪያ ልጥ እያቀበሉዋቸው፣ ሴቶቹ በዋናነት ገልማውን ሠሩ፡፡ በዚህን ጊዜ ሴቶቹ ካርሌ ማዜም (kaarilee dhaahatu) ጀመሩ፡፡ ካርሌ የዜማ ስም ነው፡፡ሴቶች ሁልጊዜ ቤት ሲሠሩ የተለያየ የካርሌ ዜማ ያዜማሉ፡፡ በገልማው ሥራ ላይ ሲያዜሙት የነበረው፣

Abbaa jilaa taatee, harka lichoon daaxxee ባለጉዳይ ሆነህ እጅህ በሊቾ ደመቀ
Abbaa biyyaa taatee dubbiin sibarbaaddee ባለ ሀገር ሆነህ ጉዳይ ሁሉ አንተን አለ

የሚል ነው፡፡ የነዚህ ስንኞች ይዘት ማሞገስ ነው፡፡

ለገልማው ሥራ ተቆርጦ የመጣው እንጨት በሙሉ ተሠርቶበት ሲያልቅ፣ በገልማ ሥራ ዋዜማ እለት መጀመሪያ ተቆርጠው የመጡት ሁለቱ የወዴሣ እንጨት እዚያው ቀሩ፡፡ በዓሉ በሚያበቃበት ሦስተኛው ቀን ወደ ገልማው ይገባሉ ተባለ፡፡

በዚህ በሁለተኛውም ቀን የበዓሉ ባለቤቶች (Warra jilaa) ከብት አርደው ወተት በብዛት ተዘጋጅቶ የበዓሉ ተሳታፊዎች ሁሉ ተጋበዙ፡፡ ከግብዣው በተጨማሪ ሴቶቹን ፀጉራቸውን ቅቤ ቀቡዋቸው፡፡ ቅቤ የመቀባቱ ድርጊት ላደረጉት አስተዋፅኦ ምስጋና የማቅረቢያ አንዱ መንገድ ስለሆነ ነው፡፡[24]

በዚህ ገልማው መሠራት በጀመረበት ዕለት ከሰዓት በኋላ ኩቹ (Kuchuu) የተባሉ ወጣቶች (በአንድ የእድሜ ክልል ያሉ) ትልቅ ወፍራም እንጨት ቆርጠው አምጥተው በማገዶም አዳራሹን ለሁለት ከፍሉት፡፡ ይህ ሂደት አዳራሹን መክፈል "Gulantaa baasuu" ይባላል። ክፍል መለየት

---

[24] ከሹ አባ ሩፉ /ሃደ ጅላ/፣ ቃለመጠይቅ፣ሰኔ 14 ቀን 1999 ፡፡

እንደማለት ነው፡፡ ይህም የተደረገው ለስም ስያሜው ቦታ ለማመቻቸት ሲሆን እንግዳ በውስጡ እንዲስተናገድ ወንበር ገብቶ፣ የምድጃ ቦታ ተዘጋጅቶ እሳት መንደድ በዚሁ እለት ጀመረ፡፡

**2.2.2.1.3. "ጂላ ጉዳ" Jila guddaa/Galma afaan goodan/ የበዓሉ ሦስተኛው ቀን**

ሦስተኛው ቀን የበዓሉ ማጠናቀቂያ ቀን ነው፡፡ ገልመ አፋን ጎደን የሚለው የኦሮምኛ ቃል በቦረናዎች ገልማው በር የሚበጅለት ዕለት ወይም ትልቁ የበዓል ዕለት፣ የስም ስያሜው ሥርዓት የሚፈፀምበት ቀን ተብሎም ይታወቃል፡፡

በዚህ በሦስተኛው ቀን ጠዋት ከብቶች ከበረት ሳይወጡ እናትየው ለበዓሉ በሚየስፈልገው አለባበስ፣ አዛባ ካነሳች በኋላ፣ የዕለቱ ሥራ ክንዋኔ ተጀመረ፡፡ እስከ አሥር ሠዓት ድረስ የገልማው አንዳንድ ሥራዎች ተሠርተው ተጠናቀቁ፡፡ ባለጉዳዩቹ ከየአቅጣጫው የሚጉርፉትን እንግዶች እየተቀበሉ፣ ሰላምታ እየሰጡ ወደ ገልማው ይመሩዋቸዋል፡፡ የበዓሉ የመጨረሻ ቀን በመሆኑም የተጠሩት ሁሉ በዚህኛው ቀን ተሟልተው የተገኙ ይመስላል፡፡ የመጡት ሁሉ ጉማተ (ስጦታ) ይሰጣሉ፡፡ የሚያመጡት ስጦታ የተለያየ ነው፡፡ ከባለ ጉዳዩ ጋር ባለው ቅርበት፣ ግንኙነትና ውለታ መሠረት ሳይሆን አይቀርም ከፍና ዝቅ የሚለው፤ ቀንድ ከብት የሰጡም ነበሩ፡ ፡ ይህ ጉማተ ሌላ ስሙ "ሀንዱራ" (Handhuuraa) ነው፡፡ ሀንዱራ በህይውት ያሉ እንደ የቀንድ ከብት፣ በግ፣ ፍየል ያሉትን ይይዛል፡፡ መረጃ አቀባዮቹ እንደተናገሩት የበዓሉ ባለቤት ለታዳሚዎች የሚያርደው ክብት ባይኖረው እንኳን ለሀንዱራ የመጣው ከብት ታርዶ መስተንግዶው ሞቅ ያለ ይሆናል፡፡ የተረፈው ደግሞ የበዓሉ አዘጋጆች ንብረት ሆኖ ምጣኔ ሀብታቸውን ያደራጁበታል፡፡

አመሻሽ ላይ ከኩሬ ውሃ (Bishaa Haaroo) በግመል ተጭኖ መጥቶ፣ አባትየው ፀጉሩን ከኩሬ በመጣው ውሃ እየተነከረ ተላጨ፡፡ መላጨት ከነበረበት ደረጃ መሻገሩን ማሳያ ነው፡፡ ይኸውም በኩር ወንድ ልጅ ስም ማሰየም ነው፡፡ ይህ ደግሞ በባህሉ ትልቅ ደረጃ ነው፡፡ለማህበረሰቡ አንድ አባል ማበርከት ነው፡፡የላጨችውም ባለቤቱ ናት፡፡ ጉዳዩ የጋራ ስለሆነ ነው ሚስቱ የምትላጨው፡፡ ሲላጭ ፀጉሩ ሙሉ በሙሉ ሙልጭ ተደርጎ አልነበርም፡፡ በጣም አነስተኛ የሆነ ፀጉር አናቱ ላይ እንዲቀር ተደረገ፡፡ይህ ሳይላጭ የቀረው ፀጉር ጉቱ (Guutuu) በመባል ይታወቃል፡፡ ጉቱ ማለት ሙሉ ማለት፡፡ ቁንጮ የሚለውንም ይተካል ጉቱ ማስቀረት ወንድ የበኩር ልጅ አባትነት ምልክት ነው፡፡ ይህ ጉቱ፣ ሰውየው የገዳ ሥርዓት ደረጃዎችን አልፎ

ጡረታ ክልል እስከሚገባ ጊዜ ድረስ ከሌላው ፀጉሩ ረዘም ብሎ በመታየት ይቆያል፡፡ የገዳ ሥርዓት ደረጃዎችን ሲጨርስ ልክ እንደ ጉቢሣ፣ በዓል ተዘጋጅቶለት ገደሞጂ ተብሎ ፀጉሩን ሙሉ በሙሉ ተላጭቶ ጡረታ ዕድሜ ውስጥ ይገባል፡፡ ፀጉር መላጨት ከአንድ ደረጃ ወደ ተከታዩ መሸጋገርን ያመለክታልና[25]

ቦርቦር ቡሌ እንደገለፁት "ጉቱ" ሁለት መልክ አለው፡፡ አንዱ የጀግንነት ሌላው የታላቅ ወንድ ልጅ አባት መግለጫ ነው፡፡ ሁለቱ ተለያይተው የሚታወቁበት ገፅታም አላቸው፡፡ የጀግንነቱ አመልካች ጉቱው ላይ ቀይ ክር ይታሰራል፡፡ የታላቅ ወንድ ልጁ አባት መሆኑን ለመግለፅ የቀረው ጉቱ ደግሞ ከመደበኛው ፀጉር ረዝሞ ከመታየት ውጭ የሚታወቅበት ልዩ ምልክት የለውም፡፡ አንድ አባት ጉቱ ሊኖረው የሚችለው ለታላቅ ወንድ ልጁ የጉቢሣ በዓል አክብሮ ፀጉሩን ተላጭቶ አስቀርቶት ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

በዚሁ በአመሻሹ ሰዓት ከብቶች ወደ በረት ገብተው ከታለቡ በኋላ ስም የሚሰየምለት ልጅ በገልማው በር ላይ ተቀምጦ አባትየው ፀጉሩን ላጨው፡፡ ሲላጨው የታለበው ትኩስ ወተትና ከኩሬ የመጣው ውሃ ተቀላቅሎ ፀጉሩን በማራስ ነው፡፡ ሁለተኛውንም ልጅ በተመሳሳይ ሁኔታ ላጨው፡፡ አለሚጨጨቱ ሙልጭ (ፅድት) ተደርጎ አይደለም ፡፡ወዲያ ወዲህ በማስመር ዓይነት ነው። ቦርቦር ቡሌና ካሉ ጂሎ እንደገለፁልኝ መስመር መስመር አድርጎ መላጨት የጉቢሣ በዓል ባለቤትነቱን ለማመልከትና ከአባትየው አለሚጨጨትም እንዲለይ ነው። የመላጨት ድርጊቱ የደረጃ ለውጡን ለመግለፅ ነው፡፡ ስም ያልነበረው ልጅ ስም ሊወጣለት ነው፤ ከዚያ በኋላ ወደ ማህበረሰቡ ተቀላቀለ ማለት ነው፡፡ ሙልጭ አለመድረጉ ደግሞ የስም ስያሜ ሥርዓቱ የሚያዘውና ከሌላው አለላጨት የሚለይበት ነው፡፡ የተላጨው ፀጉሩም አልተጣለም፤ ጮጮ በሚመስል ከእንጨት በተዘጋጀ ዕቃ ተቀመጠ፡፡ ሲወለድ ከታተበው እምብርቱ ሲደርቅ የሚወድቀው ክፍልም ተቀምጦ ለዚህ በዓል ቀርቧል፡፡ ይህ እትብትና የተላጨው ፀጉር በቦረና በአጠቃላይ በኦሮሞ በደረጃ ለውጥ ጊዜ  አንዱ የስጦታ ማስገኛ ዘዴ ነው፡፡ ለምሳሌ በሸዋ ኦሮሞ አንዲት ሴት ሳትዳር በፊት ሳዱላ /ቀሬ/እየተላጨች፣ዳርና ዳሩን ሹሩባ እየተሰራች ትቆያለች ፡፡ ከተዳረች በኋላ ግን በበሏ ቤት ዝግጅት ተደርጎ ከሳዱላዋ አካባቢ ፀጉር ተቆርጦ /ተላጭቶ/በላም ጀርባ ላይ ይደረግና ያቺ ላም ትስጣታለች። ይህ ሥርዓት ቀሬ ቡሱ/ቀሬ ዱቹ/ይባላል፡፡ በአማርኛ ሳዱላ ማስደፈን ማለት ነው፡፡ ከእምብርት ላይ የሚወደቀው

[25] ካሉ ጂሎ፣ቃለ መጠይቅ ሰኔ 12 ቀን 1999 ፡፡

እትብትም እንዲሁ የባለቤትነት መግልጫ ስለሆነ አይጣልም ስጦታ መጠየቂያ ወይም መስጫ ነው፡፡ እንደመድሃኒት የሚቆጠርበት አካባቢም አለ፡፡ ለሆድ ቁርጠት መከላከያ በአንገት ይታሰራል፡፡[26] የአባሩፋ ልጆች ከተላጩ በኋላ በእጃቸውና በአንገታቸው ላይ ከነሀስ መስል ብረት የተዘጋጁ ጌጣጌጦች ተደረጉላቸው፡፡

ከፀጉር መላጨቱ ቀጥሎ ምሽቱን ከሚከወኑ የዕለቱ ስራዎች የመጀመሪያው ቶርበን ጅላዎቹ "ቆቲ"(Qotii) ለመቁረጥ ወደ ደን መጓዝ ነው፡፡ ቆቲን ቦረናዎች የበዓል እንጨት (muka jilaa) ይሉታል፡፡ ቆቲ የእንጨት የወግ ስሙ ሲሆን በእንጨትነቱ ሚኤሣ (Mi'eessaa) የሚል ስም አለው፡፡

በመረሃ ግብሩ መሠረት ቶርበን ጅላዎቹ ቆቲ ለመቁረጥ ጫካ ገቡ፣ የቆቲ እንጨት በጫካው በብዛት ነበር፡፡ ሆኖም መጀመሪያ ላይ ያዩትን ቆቲ አልቆረጡም፡፡ ደራራ የተባለ (ወተት) በስሩ አፍስሰው አለፉ፡፡ ይህ ድርጊት ወዮምሱ (Wayyoomsuu) ይባላል፡፡ ማክበር ማለት ነው። ይህ የሚደረገው እንጨቱን እንዳአዩ መቁረጡ ማስደንገጥ ስለሚሆን ለማክበር ነው፡፡[27] ከዚያ በኋላ የሚገኘውን ቆቲ መጀመሪያ ሰንዝሮ የቆረጠው ቀደዱ ተብሎ የመሪነት ቦታ የተሰጠው ሰው ነው፡፡ ሌሎቹ እርሱን አገዙት፡፡ ቆቲን የመቁረጥ ሂደት፣ ተከታዩ ክዋኔ ስም የማውጣት ስነሥርዓት መሆኑን ይጠቁማል፡፡ በጉቢሣ የስም ስያሜ ሥርዓት ቆቲ ሳይቆረጥ ስም ማውጣት አይቻልም፡፡ በማስከተል ቆቲውን ቆርጠው በአባጅላው መሪነት እያዜሙ ተመለሱ፡፡ ዜማዎቹ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው መቅረብ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ቆቲውን ተሸከመው አዳራሹ በር እስከሚደርሱ ድረስ ሁለት ዜማዎች ብቻ አቀረቡ፡፡ የመጀመሪያው ኢያንገሎ ቲያ ኤጊ (Iyyaan galoo tiyya eegi) የሚለው ነው፡፡

| | |
|---|---|
| Iyyaan galoo tiyya eega | ተጫዋቹን እጠብቃለሁ |
| Haagaloo qabatee | ሃገሎ በአንገቱ አንጠልጥሎ |
| Simphirree gaadatee | ወፍ በወንጭፍ ይመታል |
| Haagaloon qilliftee | ሀገሎ አቃጨለች |
| Taphaa bakkaafatee | ተጫወተ እየተንገዳገደ |
| Caara yaabbii tika eega | ጥጃ እየጠበቀ (እየተንጫጩ ጥጃ ይጠብቃሉ) |
| Diidaa Baaraa qotee | ከሜዳው "ባራ" ቆፍሮ /ባራ የሚበላ ሥር/ |
| Baree quandhii kuttee | ወፍሮ የእጁ ላይ እስር ሰረሰረው |

[26] አለማየሁ ኃይሌ፣ቃለመጠይቅ፣ ስልክ፣ታህሣሥ 3 ቀነቀ 2000
[27]ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 15 ቀን 1999

በዚህ ግጥም ውስጥ ህፃናት ደጃፍ ላይ መዳህ ከጀመሩበት አንስቶ ከብቶች አግደው ለቤተሰቦቻቸው አገልግሎት የሚሰጡበት ድረስ የሚያሳዩትን ባህሪና አካላዊ እንቅስቃሴ ያስጨብጣል፡፡ከግጥሙ አንዳንድ ስንኝ ወስዶ መተንተኑ አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ ስንኝ የየራሱ ፍች አለውና፡፡ ለምሳሌ "Haagaloo qabatee" - የሚለውን ስንኝ ብንመለከት Haagaloo - ቃጭል መሰል ድምጽ የሚሰጥ ቁስ ነው፡፡ በቦረና በገጠሩ ክፍል ቁጥቋጦ በበዛበት ልጆች ከቤት ወጥተው ሲጫወቱ ሳያውቁ ርቀው እንዳይሄዱና እንዳይጠፉ ዱካቸውን ለመያዝ /ለመከተል/ አንገታቸው ላይ "ሀገሉ ይታሰርላቸዋል፡፡ ወዲያና ወዲህ ሮጠው ሲጫወቱ ድምፁ ያሉበትን የሚጠቁም ስለሆነ ስለመኖራቸውና ችግር ያልደረሰባቸው መሆኑን የሚከታተሉበት ቁስና ዘዴ ነው፡፡

"Simphirree gaadatee" የሚለውም ስንኝ የራሱ መልእክት አለው፡፡ ልጁ አድጎ በሀገሎ ድምፅ ክትትል ከሚደረግለት ጥበቃ ደረጃ ሲያልፍ በአካባቢው ያሉትን እንሰሳት ይከተላል፡፡ የመጀመሪያዋ ወፍ ትሆናለች፡፡ ወፏን ቀርቦ ለመያዝ በክር ወይም በልጥ ወንጭፍ አዘጋጅቶ መትቶ ለመጣል የሚያደርገውን ጥረት ማሳያ ነው፡፡ ግጥሞቹ አነዚህን መሰል የልጆችን ከእለት እለት እንቅስቃሴና ከቤተሰባቸው ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው።

ቶርበን ጅላዎቹ ወደ በዓሉ መከወኛ መንደር ሲዳረሱ ያዜሙት በሁለተኛ ደረጃ ያለውን ቡልቱሞ ቡሌ (Bultumoo bulee) የሚባለውን ነው፡፡ ይህንንም ዜማ መሪ ሆኖ የጀመረው አባትየው ነው ሌሎቹ እየተቀበሉት አስተጋቡ፡፡ ከዚህ ባሻገር፣ በቦረና የአንድ ሰው መታደል የሚለካው ልጅ ወልዶ ስም ለመሰየም መድረስ ስለሆነ አባትየው ይህን ዜማ ሲያሰማ “እኔ ለዚህ ዕድል በቅቻለሁ፣ እድለኛ ነኝ በፈጣሪ (አምላክ) የተሰፋ ስፍራ አድሬአለሁ” እንደማለት ነው፡፡[28]

ዜማዎቹን እያደመቁ ቆቲውን ተሸክመው ከበዓሉ በር ላይ ደረሱ፡፡ ቀጥሎም ቆቲውን በበረቱ መግቢያ ግራና ቀኝ፣ በገልማው በግራና ቀኝ፣ ከገልማው ጎን ካለው ቤት ደጃፍ፣ ገልማው ውስጥ ገብተው አለፍ አለፍ ብለው ወደ ዓዳ መግቢያ፣ ምሰሶ አካባቢ ቆፍረው ተከሉ፡፡ ጃተኒ ዲዳ አንዳሉት የቆቲው ቅጠል ጠውልጎ እስከ ሚረግፍ የልጁ ወላጆች ከገልማው ወደ ሌላ አካባቢና ቤት አይሄዱም ( አይዛወሩም)፡፡

---

[28] (ሰለሞን ጎዳና ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 22 ቀን 1999)

ከዚህ ክዋኔ በኋላ ቶበርን ጅላዎቹ ከልጁ ወላጆች፣ አያቶች ጋር በገልማው ውስጥ በተዘጋጀው የእሳት ማንደጃ ቦታ ላይ ስም ለማውጣት ተዘጋጁ፡፡ አቀማመጣቸው ሥርዓት አለው፡፡ አባትየው ልጁን አቅፎ በስተቀኝ ተቀመጠ፡፡ እናትየው ከእርሱ ለጠቀች፣ አያትየዋ በስተግራ በኩል ተቀመጡ፡፡ ወንድ አያት የሉም፡፡

ቀጥሎ አባት ለልጁ እንዲወጣለት የመረጡትን ስም፣ ከራሳቸው ስም ጋር በማጣመር አቀረቡ፡፡ አብ አባሩፋ ጃተኒ ለልጃቸው የአያት ስም ለመሰየም ስለወሰኑ "ጃተኒ አባሩፋ በሉ" ሲሉ አያቶቹ ቶርበን ጂላዎቹና በገልማው የተገኙ ታዳሚዎች በመንደሩ ተመሳሳይ ስም ያላቸውን፣ እናት አባታቸው በህይወት ያሉትን ሦስት ልጆች ስም አከታትለው ሦስት ጊዜ ጠሩ፡፡ የልጁ ስም እስከ አያቱ ድረስ ሲጠራ ጃተኒ አባሩፋ ጃተኒ ሆነ፡፡ አስከትለውም" Abbiyyeefi haadhakee bulfadhu, loon guddoo bobbaasii, jabbiyyoo guddoo tissi" አሉ፡፡ "እናት አባትህን ያቆይልህ፣ ብዙ ከብቶች አሠማራ፣ ብዙ ጥጆች አግድ"ማለት ነው፡፡ በዚሁ ለልጁ የተመረጠለት ስም ፀደቀ፡፡ የአባሩፋ ታናሽ ልጅም በዚሁ በበከሩ ልጅ ስም ስያሜ በዓል ላይ ለመሰየም ተዘጋጅቶ ስለነበር፣ በተመሳሳይ ክዋኔ ተሰየመ፡፡ እርሱንም አባትየው ታቅፎ" አብዱብ አባሩፋ በሉ" ቶርበን ጂላዎቹና በገልማው ውስጥ ያሉትም ተመሳሳይ ስም ያላቸውን የሚያውቁ ደግመው ጠርተው፣ እንደ በኩሩ፣ " Abbiyyeefi haadhakee bulfadhu, loon guddoo bobbaasii, jabbiyyoo guddoo tissi" አሉ፡፡ የርሱም ስም ፀደቀለት፡፡ አብዱብ አባሩፋ ጃተኒ ሆነ፡፡ አባትየው ካሰየመ በኋላ እናትየውም በኩሩንም ታናሽየውንም በተመሳሳይ ሁኔታ ታቅፋ ያጩላቸውን ስም እየጠራች አሰየመች፡፡

የሁለቱም ስም በአባትና እናት አቅራቢነት፣ በቶርበን ጂላዎቹ እና ታዳሚዎች አስተጋቢነት ፀደቀ፡፡በቦራና የየትኛውም ልጅ(ታላቅ፣ ታናሽ፣ ሴት) ስም ሲሰየም መነሻ የሚያደርጉት ቤተሰቡ የነበረበትን ሁኔታ፣ ልጁ(ልጅቱ) የተወለደበት/የተወለደችበት ቦታ፣ ጊዜና ወቅት ነው፡፡ የጎሳ፣ የበዓላት መከበሪያ ቦታዎችና የታወቁ ሰዎች(አባገዳዎች) ስምንም ለልጆቻቸው ይሰይማሉ፡፡ ለምሳሌ ልጁ የተወለደበትን ጊዜ /ወቅት ያደረገ ስም፡

| | |
|---|---|
| Boruu (ቦሩ) | ጠዋት የተወለደ |
| Galgaloo (ገልገሎ) | ማታ የተወለደ |
| Guyyoo (ጉዮ) | ቀን የተወለደ |

Wariyoo (ዋሪዮ) ምሽት የተወለደ

ልጁ በሚወለድበት ጊዜ ባለው ሁኔታ ተመስርተውም ስም ይሰይማሉ፡፡

ለምሳሌ

Godana (ጎዳና) አካባቢ ለቀው ሲሄዱ

Bonayaa (ቦነያ) ደረቅ ወቅት

የገዳ ሥርዓት መከወኛ ቦታዎች የበኩር ልጅ ስም ሆነው ይመረጣሉ፡፡

ለምሳሌ

Liiban (ሊበን) Gayyoo (ጋዮ) Nuuraa (ኑራ) Areeroo (አሬሮ) Doyyoo (ዶዮ)

ከስም ስያሜው ቀጥሎ ቡነ ደሃ (buna dhahaa) የተባለ ሥነስርዓት ተከናወነ፡፡ አስራ አራት ፍሬ ቡና (Torban lama) ተቆጥሮ ዙሪያውን ከበው ለስም ስያሜ በተቀመጡበት በረመጥ (ፍም) በተሞላ ምድጃ ውስጥ ጨመሩት፡፡ ቡናውን ቆጥረው የጨመሩት ከቤተሰብ አንዲት ሴት ናቸው፡፡ ሲንጣጣ አወጥተው፣ ታልቦ በቀረበ ትኩስ ወተት ውስጥ ጨመሩት፡፡ ከዚያ ቶርበን ጅላዎቹ እየተቀባበሉ ወተቱን እየተጎነጩ ሁለት ሁለት ፍሬ ቡና ከውስጡ ወስደው አኘኩ፡፡

ጃተኒ ዲዳ በገለፁት መሰረት ይህ ቡነ ደሃ ሥርዓት በሌሎችም በዓላት ላይ ይከናወናል፡፡ ሰው ሲሞትም ይደረጋል፡፡ የሚጨመረው የቡና ፍሬ ብዛት ግን ይለያያል፡፡ ይህ ሥርዓት ሰፊ ፍች አለው፡፡ በቦረና ኦሮሞ ቡና ከፈጣሪ የተሰጠ ነው፣ በህዝብ ይመሰላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ቡና መጀመሪያ በቦረናዎች ዘንድ ጥቅም ላይ ሲውል የመገልገያ ቁሳቁሶች ባለመኖራቸው የቡናን ፍሬ ቆጥረው በእሳት ፍም ውስጥ አብስለው ወተት ውስጥ በመጨመር ይቃመሱ ነበር፡፡ ያንን የጥንቱን አጠቃቀምና ተምሳሌትንቱን ለማስታወስ በትላልቅ የሽግግር ክዋኔዎች የጉቢሣ፣ የጋብቻ፣ የሞት ወቅት፣ ቡና ደሃ ብለው ይከውኑታል።

ከቡና ደሃ (Buna dhahaa) ሥነሥርዓት በኋላ "ሆ! ሃሩሶ" የሚል መግቢያ ዜማ ብለው ቆቲ ቆርጠው ሲመለሱ ካዜሙዋቸው ኢያንገሎና ቡሉቱሞ ቡሌ ጀምረው ስድስት የሚሆኑ ዜማዎችን አከታትለው አሰሙ፡፡ እነዚህ ስድስት ዜማዎች ለጉቢሣ በዓል ብቻ የሚዜሙ መሆናቸውን

አራቱም የመረጃ አቀባዮች[29] አረጋግጠውልኛል፡፡ ቀደም ሲል ቆቲ ቆርጠው ሲመለሱ ካቀረቡዋቸው ከሁለቱ ተከትለው የቀረቡት "ሰገዴ መለዮ" (Sagadde Mallayyoo), " አሸኔ ዶዮ " (Ashanee Dooyyoo)፣ " ኢልሜ ሆዮ "( Ilmee hoo yoo) እና "ሙዳ " (Muudaa)፣ የተሰኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ተዚመው ሲያበቁ፣ ከቶበርን ጅላ፣ እናትና አባት እና አያቶች በቀር የተቀሩት ታዳሚዎች ወዲያና ወዲህ ተዘዋውረው የፈለጉትን ዜማ እያዜሙ መጨፈር፣ መደሰት ጀመሩ፡፡

ከሌሊቱ ከስምንት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ባለው ጊዜ ኩቼ የሚል ስያሜ ያላቸው ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት በላይ የሆኑ ወጣቶች በረት በር ላይ ተሰብስበው በበዓሉ ላይ ለእነርሱ ተብሎ የሚዘጋጀውን ኮቼ (Kochee) የሚባለው የምግብ ዓይነት እንዲቀርብላቸው የምግቡን ማቅረቢያ ባህላዊ ዕቃ "ዲቤ (Dibbee) " ይሰጠን እያሉ በዘፈን መጠየቅ ጀመሩ፡፡ እነዚህ ወጣቶች በሁለት ቦታ ተከፍለው ለየብቻ ሲዘፍኑ ስለነበር ቶሎ አልተሰጣቸውም፡፡ ገልማ ውስጥ፤ "የተዘጋጀው በአንድ ዕቃ ነው እንዴት እናድርግ? አሁን ለአንዱ ቡድን ቢሰጥ ይጣሉበታል፡፡" ይባባሉ ነበር፡፡

ኩቼዎች፣ ኮቼ ጠይቀው በሥርዓቱ ሲሰጣቸው መርቀው ተከፋፍለው ይበላሉ፡፡ በክፍፍሉ ላይ አለመስማማት ቢፈጠር ተኮራርፈው አይለያዩም፡፡ በትግል ይዋጣልን ተባብለው፣ ታግለው አሸናፊው ታውቆ በዕርቅ ይለያያሉ[30] ወጣቶቹ ለመጣላት ሙከራ አድርገው ነበር፡፡ ግን አንዳንድ ሰዎች መሀል ገብተው አስማሙዋቸው፡፡ ቡድን ለይተው መጫወትና መጠየቅ ትተው፣ አንድነት ፈጥረው ቀረቡ ኮቼው ከነዲቤው ተሰጣቸው፡፡ ተከፋፍለው በልተው ወደ ጭፈራቸው አመሩ፡፡

በዚህ በሦስተኛው ቀን ሌሊቱን ሙሉ መኝታ ይዞ የተኛ ሰው የለም፡፡ ቶርበን ጅላዎችና የልጁ ቤተሰቦችም በገልማው ውስጥ ነው የቆዩት፡፡ በስም ስያሜው ሥነሥርዓት መሠረት እስከ አስራ አንድ ሰዓት ድረስ ለስም ስያሜ ከተቀመጡበት አይነሱም፡፡ ህፃናትም ቢያንቀላፉ በዕቅፍ ይቆያሉ እንጂ መኝታ ይዘው አይተኙም፡፡ በውስጣቸው መች ይነጋልን እያሰቡ፣ በጫወታ በጭፈራ ያሳልፋሉ፡፡ የንጋት ኮከብ ታይታ የሜዲቻ ከብት (horii meedhichaa) እርድ ለመፈፀም ጥድፊያ አለ፡፡ በመሀል አደናቃፊ መንፈስ እንዳይኖር ይፈራል፡፡ የስም ስያሜው በዓል

---

[29] አብ ቦርቦር ቡሌ፣ አብ ካሉ ጂሎ፣ አብ ጃተኒ ዲዳና አብ ሰለሞን ጎዳና

[30] ሀሮ ኤሌማ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 15 ቀን 1999፡፡

ፍፃሜ ማረጋገጫው እርዱ ነውና[31] ሊነጋጋ ሲል፣ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ "ሆሪሜዲቻ" ( Horii meedhichaa) ለማረድ ዝግጅት ተደረገ፡፡ ቶርበን ጅላዎቹ ሊታረድ የተዘጋጀውን ከብት ከበረቱ እንዳለ ለማረጋገጥ ሦስት ጊዜ ተመላልሰው በአባጂላው መሪነት አዩ፡፡ ይህ የዕርድ ሥርዓት ከጉቢሣ በዓል ከዋኔዎች የግድ የሆነ ነው፡፡ ተመላልሰው አይተው መኖሩን ካረጋገጡ በኋላ ቶርበን ጅላዎቹ፣ ሀዩዎቹ፣ አያቶቹ፣ የቅርብ ቤተሰብ የሆነ ሁሉ የበሬውን ጀርባ በሊቾ፣ በእጅ እየዳሰሱ ተራ በተራ መረቁ፡፡ ይህን ድርጊት አሬሪ ( Areerii) ይሉታል፡፡ ከተመረቀ በኋላ የበሬውን ቀንድ የልጁ አባት ይዞ ሌሎችም አግዘው ከጣሉት በኋላ ቀደዱው በሬውን አረደ።

ከዚህ የከብት እርድ በጣም ተፈላጊውና ባህላዊው ጉዳይ ከስጋው ይልቅ በቆዳው ላይ ይመሠረታል፡፡ በሬው ታርዶ እንደተንጋለለ ከእንብርቱ ዙሪያ ቆዳ ተቀፎ ወጥቶ በአባትየው እጅ ላይ ተጠለቀለት፡፡ ከዚያው በእንብርት ዙሪያ ካለው ቆዳ እንደገና ተቀፍፎ ለእናት በአንገቷ ላይ እንድታጠልቅ ተደረገ፡፡ ይህ ሜዲቻ ይባላል፡፡ የሚታረደው በሬ እራሱ የሜዲቻ ከብት በሚል ስያሜ ነው የሚታወቀው ( የሚጠራው)፡፡ አብ ጃተኒ ዲዳ እንዳሉት፣ በቦረና ባጠቃላይ በኦሮሞ፣ እምብርት ልዩ ትርጉም አለው፡፡ እምብርት መነሻና መድረሻ ነው ተብሎ ስለሚታመንበት ታላቅነት፣ የንብረት ባለቤትነት ይገለፅበታል፡፡ ለዚህም ነው የጉቢሣ በዓል ባለቤቶች አባትና እናት የታላቅ ልጃቸው በዓል መሆኑን ለመግለፅ ከእንብርት ዙሪያ ተቀፍፎ የተዘጋጀው ሜዲቻ በእጅና በአንገት ላይ የተጠለቀላቸው፡፡

ቀጥሎ ከበሬው ቁርጭምጭሚት አካባቢ ቆዳ በቀጭን በቀጭኑ ተተልትሎ አባትየው፣ ስም የተሰየመላቸው ታላቅና ታናሽ ልጆች፣ ቶርበን ጅላዎቹ በእጃቸው ላይ አጠለቁ፡፡ የቀረው ቆዳ በቀጫጭኑ ተሰንጥቆ በ"ጋዲ (Gaadii) " ስም ጉማታ ላመጡ እንግዶች ተከፋፈለ፡፡ ጋዲ ላም ሲትታለብ የኋላ እግሮቿ አንድላይ የሚታሰርበት ቁስ ነው። የከብት አርቢነት ምልክት ነው።

የታረደው ከብት ሥጋም ተከፋፍሎ ጉማተ ባመጡ ሰዎች ዕቃ ውስጥ ተከቶ ሲሄዱ እንዲወስዱ ተዘጋጀ፡፡ ይህ ጉማተ የመጣበት ዕቃ ባዶ እንዳይመለስ ተብሎ የሚሰጥበት ሁኔታ "ጉማ" ተብሎ ይታወቃል፡፡ አብ ሰለሞን ጎዳና እንዳሉት፣ ጎማተ በመጣበት ዕቃ ከትቶ መመለስ መረዳዳት፣ መተጋገዝ ሲያስፈልግ አብረን ነን ማለት ነው፡፡ ብድር መላሽ ያድርገኝ አይነት መልዕክት አለው፡፡

[31] ካሉ ጂሎ፣ ቃለ መጠይቅ ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም ፡፡

የሥጋው አከፋፈል ሲጀመር፣ የበሬውን ቀኝ እጅ ለ "ዋታ"፣ አንድ ታፋ ለ "ቱምቱ" በገልማው በር በኩል ጣራው ላይ እንዲቀመጥ ከተደረገ በኋላ ነው የተረፈው በየዕቃው የተከተተው፡፡ ዋታ የቦረና ኦሮሞ አባላት የሆኑና በአዳኝነት የሚታወቁ ናቸው፡፡ Tumtuu(ቀጥቃጭ) የተለያዩ ከብረታ ብረት የሚሠሩ ጌጣጌጥ የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ ይህ የሜዲቻ በሬ ስጋ የሚሰጣቸው፣ ዋታ የልጅ ፀጉር የሚከተትበት እንደ ጮጮ የመሰለ እንጨት ስለሚያዘጋጁ፣ ቱምቱ በልጁ እጅና አንገት ላይ የሚደረግ እንደ ካቴና የሚታይ የእጅና የአንገት ጌጥ ስለሚያዘጋጁና የስም ስያሜው በዓል ተሳታፊ ስለሆኑ ነው[32]

ከነጋ በኋላ ጠዋት ላይ፣ ቀደም ሲል ደርቆ ሲወድቅ ያስቀመጡትን የተሰያሚዎቹን ልጆች እትብትና የተላጨ ፀጉራቸውን አንድነት በጮጮ ውስጥ አድርገው ውሃና ወተት ጨምረውበት አቀረቡ፡፡ ሁለት ላሞች ከነጥጆቻቸው ተነድተው መጥተው፣ የልጆቹ ፀጉርና እትብት የተቀላቀለበት ወተትና ውሃ በላሞቹና ጥጃዎቹ ጀርባ ላይ ፈሰስ ተደረገ። አብ ጃተኒ ዲዳ እንደተናገሩት የዚህ ድርጊት ሂደት "ሀንዱራ" (Handhuuraa) ይባላል፡፡ ከብቶቹም ሀንዱራ ተብለው ይጠራሉ፡፡ ሀንዱራ ማለት ስጦታ እንደማለት ነው፡፡ የልጆችን እትብትና ፀጉር በከብቶቹ ጀርባ ላይ ማድረግ ከዛሬ ጀምሮ የናንተ ንብረቶች ናቸው ማለት ነው፡፡ ሀንዱራ የባለቤትነት መግለጫ ወይም ማመልከቻ ነው፡፡ በአማርኛ "እትብቴ የተቀበረበት ቦታ፣ የኔ የግሌ፣ ሀገሬ" እንደሚባለው፣ ከእምብርት ደርቆ የሚወድቀውን ቆዳ ለይቶ ለስጦታ ብሎ ማስቀመጥ በቦረና የባለቤትነት ማረጋገጫ ቁስ በመሆኑ ነው፡፡ ሁለቱም የተሰየሙ ታላቅና ታናሽ ልጆች የተሰጡዋቸው ከብቶች እየነዱ በረቱ ውስጥ ሶስት ጊዜ ገብተው ወጡ፡፡ ሦስት ጊዜ ገብተው መውጣታቸው፣ በእነዚህ የሥጦታ ከብቶች ቤተሰብ እናስተዳድራለን ማለት ነው፡፡ በዚህ ሂደት ሦስት ቁጥር አባትና እናት ልጅን ለመወከል ይውላል፡፡ ማለትም ልጁ አድጎ አግብቶ፣ ወልዶ አባወራ ይሆናል፡፡ በስጦታው ያስተዳድራል ነው፡፡ በጉቢሣ በዓል ላይ ብዙውን ጊዜ ጊደሮች ተመርጠው ይሰጣሉ፡፡ ጊደሮችን ብቻ መርጦ መስጠቱም ጊደሮች ወደፊት ተራብተው ልጁን ባለብዙ ከብት ሊያደርጉት ይችላሉ ለማለት ነው፡፡ በስም ስያሜው በዓል ላይ የመጡ ስጦታዎች በሙሉ ሀንዱራ በመባል ይታወቃሉ፡፡[33] በልጁ ስም በመምጣታቸውም እንደራሱ ንብረት ይቆጠራሉ፡፡ የሀንዱራ ከብቶችና ቀደም ሲል አባትየው በተለያየ ምክንያት

---

[32] ገልገሎ ዶዮ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 17 ቀን 1999

[33] ደበሶ አዲ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 17 ቀን 1999

የሰጠው የከብት ስጦታ፣ ተራብተው ከተበራከቱት ጭምር ትዳር መስርቶ ጎጆ እስከሚወጣ ድረስ ሀብትነቱ የአባት ነው፡፡[34]

ልጆቹ የሀንዱራ ከብቶች ነድተው ከተመለሱ በኋላ "Guddadha abbafi haadha keessan bulfadhaa" የሚል የመጨረሻው አጭር ምርቃት ተሰጠ፡፡ ቀጥታ ትርጉሙ እደጉ አባትና እናታችሁን አሳድሩ የሚል ነው፡፡ አድጋችሁ ለወግ ማዕረግ ደርሳችሁ ወላጆቻችሁን ለመጦር ያብቃችሁ ማለት ነው። ከዚያ በኋላ ሁሉም ወደየቤቱ ተንቀሳቀሰ፡፡ በዓሉም አበቃ፡፡

## ማጠቃለያ

በበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል(ጉቢሳ) የሦስት ቀን ቆይታ ታከታታይ ሂደት ያላቸውና ድግግሞሽ የሚታይባቸው ክዋኔዎች ተከውነዋል። ክዋኔዎቹ የደረጃ ለውጥ የሚያሳዩ ሲሆኑ በየክዋኔዎቹ በመግቢያው ውስጥ የተጠቀሱት የተለያዩ የፎክሎር ዓይነቶች ማለትም ሥነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ትውን ጥበባት ተደራርበው የሚከሰቱባቸው መሆናቸው ተረጋግጧል። እነዚህ የፎክሎር ዓይነቶች ደግሞ የህዝቡን የባህል አጠባበቅ፣ ለልጅ የሚሰጠውን ቦታ፣ እምነትና አመለካከት፣ጠንካራ የእርስበርስ ግንኙነትና መተጋገዝ የሚያሳዩ ናቸው።

ከዚህ በመነሳት እንደ ይሁንታ ልጠቅሰው የምሻው የቦረና ኦሮሞ ጉቢሣን መሰል የተለያዩ የፎክሎር ዘርፎች፣ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ እምነቱና የመሳሰሉት በተለያየ አውድ የሚከወኑና በየራሳቸው ሊጠኑ የሚችሉ እስከ ዛሬ ያልተዳሰሱ አሉት፡፡ እነዚህ የተለያዩ የፎክሎር ዝርያዎችን አካትተው የያዙ ባህላዊ ክዋኔዎች አሁንም በመከናወን ላይ ያሉ የህዝቡ ታሪክና ባህል ተጨበጭ መረጃዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ትኩረት ተሰጥቷቸው ቢጠኑ፣ ህዝቡንና አካባቢውን መሰረት አድርጎ ለሚወጠን ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሥራ መሳካት እገዛ ያደርጋሉ፡፡

[34] ቦርቦር ቤሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999

## ዋቢ መጻሕፍት

Areggaa Hailemicheal. (2005). “A Sociolingustic Approach to the Study of Anyowa Personal Names: A contribution to Socio-Onomastic Studies in a Nilo-Saharan Language.” *Ethiopian Journal of Educational researchers’Association*. A.A. Vol. 2 No1, 39-53.

Bouman, R. (1977). *Verbal Art as Performance.* Rowely Mass: Newbury House.

Dorson, Richard M.(ed) ( 1970). *Folklore and Folklife: An Inturduction*. Chicago and London: The Unicersity of Chicago Press.

Gennep, Arnold van. (1960). *The Rites of Passage.* (Translated by Monika B. Vizedom and Gabrielle L.Caffe) London, Western Printing Service,

Gluckman, Mas. (1962) *Ritual of Social Relations* (Essays) (ed) Manchester, Manchester Univesity Press.

Oromia, B. (2000). *Physical and Socio Economic Profiles of 180 Districts of Oromia Region.* Addis Ababa: Bole Printing Press.

Stephens, M. C. (2005). *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions.*Logan, Utah: Utah State University Press.

Turner, V. (1969). *The Ritual Process: Structure and Anti-Strature.* Chicago, Aldine.

ያለው እንዳወቀ ሙሉ። (2001) ። *የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*።ባህርዳር ዩነቨርስቲ፤ንግድ ማተሚያ ድርጅት።